# የአከባቢ ሳይንስ

## የመምህራን መምሪያ መጽሐፍ ሦስተኛ ክፍል


**አዘጋጆች**

ዳንኤል እንዳይላሉ　　ሀይሉ ብሩ
ገቢ ቱሲ　　ቱፋ ለሚ
ጎሳ ግርማ

**አርታኢዎች**

ጋዲሳ በዳዳ　　ቲጃኒ ሁሴን

ንጉሴ ለማ　　ዘውዱ ቱሉ

**ገምጋሚዎች**

አበራ ከበበዉ　　ከተማ ፀጋ

ተሰማ ግርማ　　ጀማል ሙስጠፋ

**ተርጓሚዎች**

በቀለ ቀነዓ　　ደረጀ መኮንን

ቡልቡሉ ዘዉዴ

**ግራፍክስ**

ታደሰ ድንቁ

**እሉስቱሬተር**

ቡዛዮ ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2021

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2021 ተዘጋጀ፡፡ የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፍቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

# ማውጫ

**ይዘት** **ገፅ**

**ምዕራፍ 1. ሳይንስን ግልፅ ማድረግ** ........ 1

1.1 ምግብና ጤንነት ........ 2

1.2 የምግብ ጥቅም ........ 5

1.3 የግል ንጽህናን መጠበቅ ........ 10

1.4 ቁስ ........ 15

1.5 የብርሃን ጥቅም ........ 21

**ምዕራፍ 2: መገኛ** ........ 24

2.1 የዞናችን መገኛ ........ 24

2.2 የአንጻራዊ መገኛ ምንነት ........ 28

2.3 ፍጹማዊ መገኛ ምንነት ........ 30

2.4 የዞናችን አንጻራዊ መገኛ ........ 34

2.6 በዞኖችን የሚገኙ ታወቂ ቦታዎች መገኛ ........ 37

2.7 የአዋሳኝ ዞኖች ስም እና መገኛ ........ 39

**ምዕራፍ 3 ተፈጥሮአዊ አካባቢያችን** ........ 42

3.1 የዞናችን የአየር ንብረት ........ 43

3.2. የተፈጥሮ ሀብት ........ 47

3.3. የተፈጥሮ ሀብት አስፈላጊነት ........ 51

3.4 ቆሻሻን ማስወገድ ........ 55

3.5 ቆሻሻ ተገቢ ባልሆነ መንገድ የመጣል ተፅዕኖ ........................................ 60

**ምዕራፍ 4 ማህበራዊ አከባቢያችን**.......................................................... 63

4.1. የአከባቢያችን የባህል ብዝሃነት ........................................................ 64

4.2 የዞንናችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ........................................................ 67

**መዕራፍ 5 ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ጉዳዮች** ................................................. 71

5.1 በመንገድ አጠቃቀም ላይ የሚደረግ ጥንቃቄ ............................................ 71

5.2 ኤች አይ አቪ /ኤድስ ........................................................................ 75

**የአካባቢ ሳይንስ መርሃ ትምህርት**.......................................................... 80

# ምዕራፍ 1. ሳይንስን ግልፅ ማድረግ

ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት .......... 24

**የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውጤቶች**

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ለጤንነት አስፈላጊ የሆኑትን የምግብና የመጠጥ አይነቶችን በመለየት ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡
- ምግቦችን በአራቱ መሠረታዊ የምግብ ምድቦች ስር ይመድባሉ፡፡
- የምግብ መበከልን ለመከላከል ቀለል ያሉትን የምግብ ንጽዕና አጠባበቅ ዘዴዎችን ይገልጻሉ፡፡
- የጠጣር ፈሳሽና ጋስ ባህሪያትና ፍቺ ይገልጻሉ፡፡
- የንጽህና አጠባበቅ ዘዴዎችን ይገልጻሉ፡፡
- የነገሮች ሁነት ለውጥን (ጠጣር ፈሳሽና ጋስ) ይገልጻሉ፡፡
- የተለያዩ የብርሃን ጥቅሞችን ይዘረዝራሉ፡፡

**መግቢያ**

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች ለጤና አስፈላጊ የሆኑትን ምግቦችና መጠጦች የምግብ ጥቅም አራቱ መሰረታዊ የምግብ ምድቦች እና የምግብ መበከል መከላከያ ዘዴዎችን ይማራሉ፡፡ ተማሪዎች የምግብና የመጠጥ ምንነትን በመገንዘብ ለጤንነት ጠቃሚ የሆኑትን ምግቦችንና መጠጦችን ለመለየት ያግዛቸዋል፡፡ እንደዚሁም፣ የምግብ መበከል መከላከያ ዘዴዎችን በማወቅ ስራ ላይ ያውላሉ፡፡ የጠጣር ፈሳሽና ጋስ ባህርይ ይገልፃሉ፣ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ ስለ ንጽህና አጠባበቅ ዘዴዎች እና የነገሮች ሁነት ለውጥና ስለ ብርሃን ጥቅሞች ይማራሉ፡፡

# 1.1 ምግብና ጤንነት

ለዚህ ትምህርት አርዕስት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት ----------------------2

**የዚህን ትምህርት ርዕስ የመማር ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ለጤና ጠቃሚ የሆኑትን ምግቦችና መጠጦችን በመለየት ሃሳብ ይሰጣሉ፡ ፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በዚህ የትምህርት ይዘት ስር ተማሪዎች ለጤና ጠቃሚ የሆኑትን የምግቦችንና የመጠጦች ዓይነትና ምንነትን ይማራሉ፡፡

ይህን ንዑስ ርዕስ ለማስተማር የመማር ማስተማር ዘዴዎችን፡- እንደ ማንበብ፣ በጥንድ መወያየት፣ በቡድን መወያየትና ገለፃን መጠቀም ይቻላል፡ ፡ ለጤና ተስማሚ የሆኑትን ምግቦችና መጠጦች ለይተው ለማወቅ እና ለጤና ተስማሚ ያልሆኑትን ምግቦችና መጠጦች እንዳይጠቀሙ ይረዳቸዋል፡፡ በተጨማሪም በሚቀጥሉት የትምህርት ክፍሎች ውስጥ ለሚሰጣቸው ትምህርት መነሻ ይሆናቸዋል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

መምህራን ክፍል ከመግባታቸዉ በፊት የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በሚዘጋጀው የትምህርት ዕቅድ ውስጥ የትምህርት ይዘቶችን በደንብ በመገንዘብ ተማሪዎችም በደንብ እንዲገነዘቡ ለማድረግ ለዚህ ንዑስ ርዕስ የሚያስፈልገውን ሁሉ ማዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ስለ ርዕሱ እውቀትና ግንዛቤ ይበልጡን ለማግኘት የተለያዩ አጋዥ መጽሐፍትን በመጠቀምና በማንበብ ራስን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን የትምህርት ይዘት ለማስተማር በአካባቢ የሚገኙትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን እንደ የምግብና የመጠጦች ፎቶ እና የመሳሰሉትን መጠቀም ይቻላል፡፡

በተጨማሪም በአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ ይህን ንዑስ ትምህርት ለማስተማር የሚያስፈለጉትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሚሰጠውን ትምህርት ተጨባጭ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

**የማማር ማስተማር ዘዴ**

ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ሁሉንም ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቅ አስፈላጊ ነው፡፡

ቅድመ ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኂላ በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎችን ማነቃቃትና ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

ሀ. ከረሜላና ብስኩት ምግቦች በብዛት መመገብ ለጤና አስፈላጊ ናቸዉ?

ለ. በጤና ላይ ምን አይነት ችግሮችን ሊያስከትሉ ይችላሉ?

ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ካደረጋችዉ በኂላ ወደ እለቱ ትምህርት መግባት ነው፡፡ በመቀጠል ተማሪዎችን በጥንድና በቡድን በመመደብ ምግብና እንዲሁም ጤና ምን እንደሆነ እርስ በራሳቸው እንዲወያዩ ማድረግ ነው፡፡ ከቡድን ውስጥ የተወሰኑት ተማሪዎች በተወያዩበት ነጥቦች ላይ በክፍል ውስጥ ገለጻ እንዲሰጡ ማድረግ፣ በመቀጠልም ተማሪዎችን አራት በአራት ሆነው ለጤናችን አስፈላጊ ያልሆኑትን ምግቦችና መጠጦችን እንዲዘረዝሩና እንዲወያዩበት ማድረግ ነው፡፡

በመቀጠል በውይይታቸው ውስጥ ለጤና ጠቃሚ ያልሆኑትን ምግቦችና መጠጦች ከዘረዘሩ በኂላ እያንዳንዳቸው ምን አይነት በሽታ ማስከተል እንደሚችሉ እንዲገልጹ ማድረግ የተወያዩበትንም በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ ነዉ፡፡ ተማሪዎቹ በሚወያዩበትና በሚገልጹበት ወቅት በመከታተል ስህተቶችን በማረምና በመጨረሻም ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት በጣም

አስፈላጊ ነው፡፡ በእያንዳንዱ የተማሪዎች ገለጻ ውስጥ አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ የማስታረቂያ ሀሳብ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

- ከእፅዋትና ከእንስሳት የሚገኙትን ምግቦች ምን ምን እንደሆኑ በመጠየቅ ክፍል ውስጥ እንዲያብራሩ ማድረግ፤
- ተማሪዎች በቡድን በመሆን በመጠኑ መጠቀም ያለብንን ምግቦች ምን ምን እንደሆኑና ስኳር የበዛባቸውን ምግቦች እንዲዘረዝሩ ማድረግ፤

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንዲኖራቸው ማበረታታት**

ልዩ የፈጠራ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎችን ለመፍጠርና ለማነቃቃት በጤና ላይ ችግር የሚያስከትሉትን ምግቦችና መጠጦችን በመለየት ምን ዓይነት በሽታን ሊያስከትኩ እንደሚችሉ እንዲገልጹ ማድረግ፤ በክፍል ውስጥ በቂ ገለጻ የሚሰጡትን ተማሪዎች ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- እንደ ከረሜላና ብስኩት ያሉትን ምግቦች በተመለከተ የተለያዩ ስዕልና ፎቶ ከትምህርቱ ዓላማና ይዘት ጋር የሚገናኙትን በመጠቀም ተማሪዎች በትምህርቱ ይዘት ላይ ያገኙትን ግንዛቤ እንዲገልጹ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች በዚህ የትምህርት ይዘት ስር ያሉትን ጥያቄዎችና ተግባራትን በሙሉ በግል ወይም በቡድን እንዲሰሩ በማድረግ የሚያደርጉትን ድርጊቶች ወይንም ውይይት በቅርበት በመከታተል ገንቢ የሆነ ግበረ መልስ መሰጠት ነው፡፡
- ጥያቄዎችንና የቤት ስራዎችን በመስጠት መከታተል፡፡
- የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ እየመዘገቡ መሄድ፡፡
- ተማሪዎቹ ላሉበት የግንዛቤ ደረጃ የማበረታቻና ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መሰጠት፡፡

**የተግባር መልስ**

ተግባር 1.1

- ለጤና ጠቃሚ የሆኑትን የምግብና የመጠጥ ምሳሌዎች ምንጮቻቸው ከእፅዋት የሆኑት የምግብ አይነቶች እንደ አትክልትና ፍራፍሬ ለጤና በጣም ጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ጣፋጭነት የሌላቸዉ ምግቦች፣ ጨውና ጮማ ያልበዛበት መመገብ ይመረጣል፡፡
- እንደ አቮካዶ ፓፓያ ማንጎና የመሳሰሉትን ጭማቂዎች እና እንዲሁም ወተትና የመሳሰሉት ፈሳሾች ለጤና አስፈላጊ ናቸው፡፡

**ለጤና ጠንቅ የሆኑ መጠጦች፡-** እንደ አልኮልና ጣፋጭ የሆኑ መጠጦች ለጤና ጠንቅ ናቸው፡፡

**ስኳር የሚበዛባቸው ምግቦች፡-** ከረሜላ፣ ኬክ፣ ብስኩት፣ ጀላቲ፣ ለስላሳ መጠጦችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

# 1.2 የምግብ ጥቅም

ለዚህ የትምህርት ይዘት የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት -------- 12

**የዚህ ትምህርት ርዕስ የመማር ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ከተማሩ በኋላ፡-

- ምግቦች በአራት መሠረታዊ የምግብ ምድቦች ይመድባሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

ምግብ ለሰውነታችን የተለያዩ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡ ምግብ ለሰውነታችን ጉልበትን ይሰጣል፡፡ እንዲሁም ስውነታችንን ለመገንባት በጣም አስፈላጊ ነው፡ ፡

በተጨማሪም ምግብ ከሰውነታችን በሽታን ለመከላከል ይረዳል፡፡ በዚህ ንዑስ የትምህርት ይዘት ተማሪዎች ከምግብ የሚገኘውን ጥቅም ይማራሉ፡፡

እንዲሁም ስለ አራቱ መሰረታዊ የምግብ ምድቦች ይማራሉ፡፡ ይህን ርዕስ በቡድንና በጥንድ በማወያየት ማስተማር ይቻላል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

ይህ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ዝግጅት ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ እለታዊ የትምህርት ዕቅድ በጥልቀት ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ የምግብን ጥቅም፣ መሰረታዊ የምግብ ምድቦች፣ ለምግብ መበከል ምክንያቶችና መከላከያ መንገዶችን ለማስተማር በቂ ዝግጅት በማድረግ ራስን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን ለማድረግም ከዚህ ርዕስ ጋር የሚገናኙትን ከተማሪዎች መጽሐፍትና ከአጋዥ መጽሐፍት በማንበብ ራስን ማዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሚከተሉትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ከአካባቢው ከሚገኙ ነገሮች በመስራት ማዘጋጀት ይጠበቃል፡፡

- ፖስተሮች ስዕሎችና ፎቶዎች
- ሌላው ደግሞ ተማሪዎች የሚጽፉበትን ፍሊፕ ቻርት
- እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በቀላሉ የሚገኙትን የምግብ ዓይነቶችን መጠቀም ይቻላል፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

በመጀመሪያ ተማሪዎች በግላቸው የምግብ ጥቅሞችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡

ሀ. ተማሪዎች በግላቸው የዘረዘሩትን የምግብ ጥቅሞችን በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ በቀረበው ማብራሪያ ላይ የማጠቃለያ ሃሳብ ማስጠት ጠቃሚ ነው፡፡

ለ. በመቀጠል ተማሪዎችን አራት በአራት በመክፈል በፍሊፕ ቻርት ላይ ሚያውቁትን የምግብ ምድቦች እንዲዘረዝሩና የምግብ አይነቶችንም በምድባቸው ስር እንዲዘረዝሩ ማበረታታት፡፡ የጻፉትን በክፈል ውስጥ እንድያቀርቡ ማድረግ፤ በቡድን ባቀረቡት ሀሳብ ላይ ግበረ መልስ መስጠት፡፡ መገንዘብ ባለበት ጽንሰ ሃሳብ ላይ በመመርኮዝ ገንቢ ግብረ መልስ በሚሰጥበት ወቅት ፖስተሮችንና ፎቶዎችን ማሳየት ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ መረዳት ይችላሉ፡፡

ሐ. ለምግብ መበከል ምክንያቶች ላይ በጥንድ ሆነው እንዲወያዩ በማድረግ ከተወያዩ በኋላ ጥንዶቹ እንደገና አራት አራት በመሆን ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ፡፡ የተወያዩበትን ነጥቦች ማስታወሻ በመያዝ ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡ ክፍል ውስጥ ካቀረቡ በኋላ በቀረበው ላይ ስህተቶች የሚኖሩ ከሆነ ማስተካከያ በመስጠት በመጨረሻም ግብረ መልስ በመስጠት ትምህርቱን መቋጨት ያስፈልጋል፡፡ የምግብ መበከል ምክንያት የሆኑትን ለማሳየት ፖስተሮችንና ፎቶዎችን በመጠቀም ትምህርቱን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ይረዳል፡፡

መ. ተማሪዎች በቡድን በመሆን በምግብ መበከል መከላከያ ዘዴዎች ላይ እንዲወያዩና እርስ በርሳቸው እንዲስማሙ ማድረግ፡፡ በቤታቸው ውሰጥ የምግብ መበከል መከላከያ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡ ተማሪዎች በሚሰጡት መግለጫ ነጥቦች ላይ ገንቢ ግብረ መልስ በመስጠት ትምህርቱን መቋጨት ነው፡፡

## 5. ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንዲኖራቸው ማበረታታት

ተማሪዎች በቡድን በመሆን የምግብና የምግብ መበከል ምክንያቶችን የሚያሳዩ ሰዕሎችን እና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በአካባቢው ከሚገኙ ነገሮች

እንዲያዘጋጁ ማበረታታት፣ ያዘጋጁትንም በክፍል ውስጥ እንዲያሳዩና አንዱ የሌላውን እንዲያይ በማድረግ ማበታታት አስፈላጊ ነው፡፤

## 6. ተከታታይ ምዘና

- የምግብ ምድቦችና የምግብ መበከል መንስኤዎችን በተመለከተ ተማሪዎች ያገኙትን እውቀት ከፖስቶተሮችና ከስዕሎች ላይ በማየት ክፈል ውስጥ እንዲገልፁ ማድረግ፡፡
- ከዚህ ርዕስ ጋር የሚገናኙትን ጥያቄዎች፣ ውይይቶችና የተለያዩ ተግባራትን ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ የተማሪዎችን ስራ በቅርበት መከታተልና ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት ነው፡፡
- ተጨማሪ ተግባራትን ለተማሪዎች በመስጠት በሚሰሩበት ወቅት ክትትል ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች ተጨባጭ ተግባራትን ሲያከናውኑ መደገፍና ማስተካከያ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡
- ተማሪዎች በፍሊፕ ቻርት ላይ የምግብ አይነቶችን በመጻፍ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ካለው ጋር ማስተያየት፡፡
- የተማሪዎችን አፈጻጸም እየመዘገቡ መሄድ፡፡
- ለተማሪዎች ስራ ገንቢ ግብረ መልስ በየጊዜው መሰጠት፡፡

### የተግባር ጥያቆች መልስ

**ተግባር 1.2**

- ዳቦና ፓስታ የሰብል አህሎች ምድብ ነዉ፡፡
- እርጎ የወተት ምድብ ነው፡፡
- የዶሮ ስጋ የሥጋ ምድብ ነው፡፡

- ቲማቲምና አቮካዶ የአትክልትና ፍራፍሬ ምድብ ነዉ፡፡

**ተግባር 1.3**

ሀ. ንፁህ ውሃ

ለ. እጃችንን መታጠብ ያለብን ጊዜ፡-

- ✓ ምግብ ከማዘጋጀታችን በፊት፣ ምግብ በሚዘጋጅበት ወቅትና ምግብ ካዘጋጀን በኋላ ነው፡፡
- ✓ ምግብ ከመመገባችን በፊትና ከተመገብን በኋላ መታጠብ አለብን፡፡
- ✓ ሽንት ቤት ከተጠቀምን በኋላ፡፡
- ✓ የታመሙትን ከጠየቅና ከቦታ ቦታ ካንቀሳቀስን በኋላ መታጠብ፡፡
- ✓ ቁስልን የነካካን ከሆነ እጃችንን መታጠብ፡፡
- ✓ ካአሳለንና ካስነጠስን በአፍንጫና በአፍ የሚወጡትን ፈሳሾች ከአጸዳን በኋላ፡፡
- ✓ ለእንስሳት ምግብ ከሰጠን በኋላ፡፡
- ✓ ምግብ የተመገብንበትን እቃዎች፣ ልብስና የመኖሪያ ቤታችንን ካጸዳን በኋላ፡፡
- ✓ እንስሳቶችን በእጃችን የምንነካካ ከሆነ፡፡
- ✓ አፈር የምንነካካ ከሆነ፡፡
- ✓ የተለያዩ ጫወታዎችን ከተጫወትንና ስፖርት ከሰራን በኋላ፡፡
- ✓ በቤተ ሙከራ ውስጥ ከሰራን በኋላ፡፡
- ✓ የቆሻሻ መጣያ እቃዎችን በአጃችን ከነካካን በኋላ እጃችንን በደንብ በሳሙናና በውሃ መታጠብ አለብን፡፡

ሐ. የእጅ መታጠብ ጥቅም፡-

- ለጤና ጠንቅ የሆኑትን ነገሮች/ጀርሞች ወደ ሰውነታችን ውስጥ እንዳይገቡ ለመከላከልና ጤናማ ለመሆን፡፡

መ. ምግብን ሊበክሉ የሚችሉ ነፍሳቶች

- ዝንብ፣ በረሮ፣ ምስጥና የመሳሰሉት ናቸው

## 1.3 የግል ንጽህናን መጠበቅ

- ለዚህ ንዑስ ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ ብዛት------- 18

**የዚህ ትምህርት ርዕስ የመማር ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህንን የትምህርት ይዘት ከተማሩ በኋላ፡-

- የንፅህና አጠባበቅ ዘዴዎችን ይገልጻሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

የግል ንጽህናን መጠበቅ ምን ጊዜም የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ ይህም፡- ሰውነታችንን መታጠብ፣ ጥርሳችንን ማፋቅና ማጽዳት፣ ጥፍራችንን በየጊዜው መቁረጥና ማፅዳት፣ ፀጉራችንን መታጠብ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የግልን ንፅህና በደንብ መጠበቅ ከተለያዩ በሽታዎች ራሳችንን እንድንጠብቅ ያግዘናል፡ የግል ንጽህናን መጠበቅ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የጎላ ሚና አለው፡፡ ንፅህናችንን ካልጠበቅን ለብዙ ዓይነት በሽታዎች ሊያጋልጠን ይችላል፡፡ በዚህ ርዕስ ሥር ተማሪዎች የግል ንጽህናን መጠበቅ ምን እንደሆነ፣ ንጽህናችንን ካልጠበቅን በሌሎች ሰዎች ላይ ምን ሊፈጠር እንደሚችል፣ በንጽህና ጉድለት ሊመጡ የሚችሉትን በሽታዎች፣ የታመሙ ሰዎችንና ጨነኞችን ማወዳደር እና ለታመሙ ሰዎች ሊደረግላቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎችን ይማራሉ፡፡

የግል ንፅህና አጠባበቅ በሚማሩበት ወቅት በኑሮኣቸው ውስጥ የግል ንጽህናን በመጠበቅ ለጤናቸው በጣም አስፈላጊ መሆኑን ይረዳሉ፡፡ የግል ንጽህናን አለመጠበቅ ደግሞ በሌሎች ሰዎች ላይ የተለያዩ ተፅዕኖዎችን እንደሚያደርስና የተለያዩ በሽታዎችን ወደ ሌሎቸ ሰዎች ለማስተላለፍ ምክንያት መሆን

እንደሚችልም ይለያሉ፡፡ በተጨማሪም በጤነኛና በታመመ ሰው መካከል ያለውን ልዩነቶችን ይለያሉ፡፡ ለታመሙት ሰዎችም አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው ይረደሉ፡፡ ይህን ንዑስ ርዕስ ለማስተማር የማማር ማስተማሪያ ዘዴዎችን እንደ የቡድን ስራ፣ የጥንድ ስራ፣ ገለፃና ፕሮጀክትን መጠቀም ይቻላል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

የዚህን ንዑስ ርዕስ ትምህርት ከመጀመርዎ በፊት በቂ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለሁሉም የትምህርት ክፍለ ጊዜ የትምህርት ዕቅድ በጥልቀት ማዘጋጀት አሰፈላጊ ነው፡፡ በዚህ አርዕስት ስር ያሉትን ጽንሰ ሀሳብን በሙሉ ለማስተማር ራስን ማዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎችን መጽሐፍትና ከዋቢ መጽሐፍት በማንበብ ራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

ይህን ርዕስ ለማስተማር የሚከተሉትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በአካባቢው ከሚገኙ ነገሮች ማዘጋጀትና መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

የግል ንጽህናን ለመጠበቅና የታመሙና ጤነኛ የሆኑትን ሰዎች የሚያሳይ ስዕሎች፣ ፎቶዎችንና ፖስተሮችን በማዘጋጀት መጠቀም፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

መምህራን ሁሉንም ቅድመ ዝግጅት ካጠናቀቁ በኋላ እያንዳንዱን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ከመጀመርዎ በፊት ተማሪዎችን የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡

ሀ. የግል ንጽህና ምንድነው?

ለ. ንጽህናችንን ካልጠበቅን በሌሎች ሰዎች ላይ የሚደርሰዉ ተጽዕኖ ምን ሊሆን ይችላል?

ሐ. በንጽህና ጉድለት የሚመጡት በሽታዎች ምን ምን ናቸው?

መ. ጤናኛና የታመሙ ሰዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ከሰጡ በኋላ ወደ እለቱ ትምህርት መግባት ያስፈልጋል፡፤

- ተማሪዎችን ሁለት በሁለት በማዘጋጀት የግል ንፅህና ምን እንደሆና እና የግል ንጽህናን ለምን እንደምንጠብቅ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ በመጨረሻም በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ፤ ተማሪዎቹ በሚወያዩበት ወቅትና በሚያቀርቡበት ወቅት ክትትል በማድረግ እርማት በሚያስፈልግበት ጊዜ ማረምና ገንቢ ግብረ መልሰ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በእያንዳንዱ የተማሪዎች ውይይትና አቅርቦት ላይ አሰፈላጊ የሆነ ገለፃ ማድረግ ነው፡፡
- ንፅህናችንን ካልጠበቅን በሌሎች ሰዎች ላይ የሚደርሱትን ተፅዕኖ ላይ እንዲወያዩና እርስ በራሳቸው እነዲመካከሩ ማድረግ እርስ በራቸው በተመካከሩበት ጉዳይ ላይ አጭር ገለጻ በመስጠት ትምህርቱን ማጠናቀቅ ያስፈልጋል፡፡
- ተማሪዎችን በቡድን በቡድን በማቀናጀት በንጽህና ጉድለት የሚመጡትን በሽታዎች እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣ ከዘረዘሩት ጋር በማገናኘት ዋና ዋና ነጥቦችን በማንሳት ማጠናቀቅ አስፈላጊ ነው፡፡
- ተማሪዎችን አራት አባላት ባለው ቡድን በማደራጀት በጤነኛና በታማሚ ሰዎች መካከል ባለው ልዩነት ላይ እንዲወያዩና ክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ በቀረቡት ላይ አጭር ገለጻና ዋና ዋና ነጥቦችን በመንሳት ትምህርቱን ማጠናቀቅ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም፤ በዚህ ርዕስ ላይ የተለያዩ ስራዎችን ለተማሪዎች መስጠት ነው፡፡
- ተማሪዎችን ጥንድ በጥንድ በመመደብ ለታመሙ ሰዎች የሚደረግላቸውን እንክብካቤና ክትትል ወይም ትኩረት ላይ እንዲወያዩ

በማድረግ ከተወያዩ በኋላ አንድ ላይ በማምጣት በቡድን ሆነው ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ የውይይታቸውን ዋና ዋና ነጥቦች በማስታወሻ ላይ በመያዝ ለሙሉ ክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግ ነው፡፡

**ተማሪዎች ልዩ የፈጠራ ችሎታ እንዲያደብሩ ማድረግ**

ልዩ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማፍራት በአካባቢው በሚገኙ ነገሮች በፍሊፕ ቻርትና በፕላስቲክ ላይ ጤናማና የታመሙ ሰዎችን ስዕል እንዲስሉና እንዲሁም በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነቶች እንዲጠቁሙ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ ለእንደዚህ አይነት ተማሪዎች የማበረታቻ ሽልማት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ጤናማና ጤናማ ባልሆኑት ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነቶችና የግል ንጽህና አጠባበቅን በተመለከተ ተማሪዎች ትምህርቱን ከዓላማና የትምህርቱ ይዘቶች ጋር በማገናኘት ስዕሎችን ፎቶዎችንና ፖስተሮችን በመጠቀም በትምህርቱ ላይ ያገኙትን እውቀት እንዲገልፁ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎቹ በዚህ ርዕስ ስር ያሉትን ጥያቄዎች ተግባራትንና ፕሮጀክቶችን በግል ወይም በቡድን በመሆን እንዲሰሩ ክትትል በማድረግ ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡
- ተጨማሪ የተለያዩ ተግባራትን ለተማሪዎች በመስጠት እንዲሰሩ መከታተል፡፡
- የተማሪዎችን ብቃት በየጊዜው እየመዘገቡ መሄድ፡፡
- በአጠቃላይ በየጊዜው ለተማሪዎች ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**የተግባራት መልስ**

**ለግንዛቤ ጥያቄዎች ተጨማሪ ገለጻ**

| ተ.ቁ | የበሽታ አይነት | የሚያጠቃው አካል |
|---|---|---|
| 1 | ታይሮይድ | የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን እንደ ጉበት፣ ሆሞት፣ ኩላሊትና ጡንቻዎችን ይጎዳል፡፡ |
| 2 | ኮሌራ | የዚህ በሽታ ባክቴሪያ ትንሹን አንጀት ያጠቃል፡፡ |
| 3 | ጉንፋን | ጉሮሮና አፍንጫን ይጎዳል፡፡ |
| 4 | እንፋሌንዛ | ጉሮሮ፣ የውስጠኛ አፍ፣ አፍንጫ፣ የአፍንጫ ቀዳዳ፣ አልፍ አልፎ የአየር ቧንቧ፣ ሳንባና የመሳሰሉትን ያጠቃል፡፡ |
| 5 | ኮሮና | ጉሮሮ፣ የውስጠኛ አፍ፣ አፍንጫ፣ የአፍንጫ ቀዳዳ፣ የአየር ቧንቧ፣ ሳንባና የመሳሰሉትን ያጠቃል፡፡ |
| 6 | ትራኮማ | አይንን በመጉዳት የአይን ህመምን ሊያስከትል ይችላል፡፡ |

**ተግባር 1.4**

1. የግል ንጽህናን መጠበቅ ሁል ጊዜ የሚተገበር ተግባር ሆኖ ሰውነታችንን መታጠብ፣ ጥርሳችንን መፋቅና ማጽዳት፣ ጥፍራችንን በየጊዜው በመቁረጥ መሳጠርና ማጽዳት፣ ፀጉራችንን መታጠብና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡
2. የፀጉራችን ንጽህና አለመጠበቅ እንደ ቅማል ላሉት ነፍሳት የመራቢያ ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡

3. በግል ንጽህና እጥረት ምክንያት ሊመጡ የሚችሉት በሽታዎች፡- ኮሌራ፣ ታይፎይድ፣ አሜባ፣ ጃርዲያ፣ ጉንፋን፣ እንፉሌንዛ፣ ኮሮና፣ የጥርስ ህመም፣ የእግር ፈንገስና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
4. ጤናማ የሆኑት ሰዎች በማህበራዊ ኑሮ ውስጥም ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የታመሙት ሰዎች የሰውነት አካላቸው በትክክል መስራት ያዳግታቸዋል፡፡ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥም በትክክል መሳተፍ አይችሉም፡፡
5. ለታመሙት ሰዎች ፍቅርን ማሳየት ሐኪም ቤት መውሰድና የመሳሰሉትን እንክብካቤ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

# 1.4 ቁስ

የጠጣር ፈሳሽና ጋስ ፍቺ ባህሪያት

ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት -------7

**የዚህ ትምህርት ርዕስ የመማር ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህን የትምህርት ርዕስ ከተማሩ በኂላ፡-

- ✓ የጠጣር፣ ፈሳሽና ጋስ ፍቺንና ባህሪያቸውን ይገልጻሉ፡፡
- ✓ የነገሮች ሁኔታ ለውጥ (ጠጣር ፈሳሽና ጋስ ) ያብራራላሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ስር የጠጣር የፈሳሽና የጋስ ፍቺና ባህሪያቸውን ይማራሉ፡፡ እንዲሁም፤ በነገሮች መካከል የሁነት ለውጥን ይለያሉ፡፡ ይህን ንዑስ ርዕስ ለማስተማር የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች፡- የቡድን ሥራና ገለጻን መጠቀም ይቻላል፡፡ በአራተኛ ክፍል ትምህርት ውስጥ ለምማሩት ስለ ፊዚካላዊና ኬሚካላዊ ቁስ አካለት ባህሪያት መሰረት ይሆናቸዋል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

መምህራን ክፍል ሳይገቡ ለሁሉም ትምህርት ክፍለ ጊዜ ዕቅድ በትክክል ማውጣትና ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡

- በዚህ ርዕስ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት የተዘጋጀውን አጋዥ መጽሐፍትን በማንበብ ግንዛቤ ማዳበር
- የጠጣር የፈሳሽና የጋስ ባህሪያትን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ማዘጋጀት
- የሁኔታ ለውጥ የሚያሳይ ስዕል ማዘጋጀት

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

ማስተማር ከመጀመራችሁ በፊት አስፈላጊውን ዝግጅት መጨረስ አስፈላጊ ነው፡፡

ሁሉም ዝግጅት ካለቀ በኋላ እያንዳንዱን ርዕስ ከማስተማር በፊት ተማሪዎችን ማነቃቃትና የትምህርት ፍላጎት እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

በቤታቸውና በትምህርት ክፍላቸው ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች እንዲዘረዝሩ በማድረግ የዘረዘሩትን ደግሞ በሁነታቸው እንዲመድቡ ማድረግ፡፡

በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮች በሶስት ሁነት (ጠጣር፣ ፈሰሽና ጋስ) እንደሚገኙ አስገንዝቡ፡፡

በመኖሪያ ቤታቸውና በትምህርት ቤታቸው የሚገኙ ነገሮች በሁነታቸው ስር ለይተው በማስታወሻቸው እንዲይዙ አድርጉ፡፡

በማስታወሻቸው የጻፉትን ከተመለከታችሁ በኋላ ከዚህ በታች ያለውን የሶስቱም ሁነት ምሳሌ የያዘውን ሠንጠረዥ በማሳየት ከራሳቸው መልስ ጋር በማነጻጸር እንዲረዱ አድርጉ፡፡

| ጠጣር | ፈሳሽ | ጋስ |
|---|---|---|
| አፈር | ውሃ | አየር |
| ድንጋይ | ወተት | የውሃ ትነት |
| ጠመኔ | ጭማቂ | ዳመና |
| እስክርቢቶ | ሻይ | ጪስ |
| መቀመጫ | ሾርባ | ንፋስ |

የሶስቱን ሁነት ባህሪያት እንዲረዱ ከዚህ በታች ያለውን ገለፃ በቡድን እንዲወያዩበትና እንዲያጤኑ ማድረግ፡፡

## የጠጣር የፈሰሽና ጋስ ባህሪያት

አንድ ነገር ከሌላው የሚለይበት የራሱ የሆነ ባህሪይ ስላለው መሆኑን አስገንዝቡ፡፡

የጠጣር፣ የፈሳሽና የጋስ ልዩነት በሞሎኪዩሎች መጠጋጋት ወይም መራራቅ የሚገለጽ መሆኑን አሰገንዝቡ፡፡ ተማሪዎች በጠጣር፣ በፈሳሽና በጋስ መካከል ባያለው ልዩነት ላይ እንዲወያዩ በቡድን በማከፋፈል ክትትል አድርጉ፡፡

ጠጣር ውስን የሆነ ቅርጽና ይዘት አለው፤ ፈሳሽ ይዘት አለው ነገር ግን የራሱ የሆነ ቅርጽ የለውም፡፡ ጋስ ይዘትም ሆነ ቅርጽ የለውም፡፡ ይህንን አስገንዝቡ፡ ፡ የተለያዩ አለቶችን በመውሰድ የጠጣርን ባህሪያትን ትልቅ መጠና ቁስ የላቸው ትንሽ መጠነ ቁስ ያላቸው በቀላሉ የሚሰበሩ እና በቀላሉ የማይሰበሩ መሆናቸውን በቡድን በማከፋፈል ጥናት እንዲያካሄዱ አበረታቱኣቸው፡፡ በመሰባበርና በመቅደድ የጠጣር የቅርጽ ሁነት መቀየር እንደሚቻል አስገንዝቡኣቸው፡፡

ያጋሶችን ባህሪያት ለማጥናት ውሃ የያዘን ባልዲና ብርጭቆ በማዘጋጀት ብርጭቆን አፉን ወደ ታች በማዞር ውሃ ውስጥ ወደ ታች እንዲገፉ በማድረግ ምን እንደተፈጠረ ጠይቋቸው፡፡

ውሃ ብርጭቆ መግባት ያልቻለው ብርጭቆ በጋሶች ስለተሞላ መሆኑን አስግንዝቡ፡፡

የጠጣር፣ የፈሳሽና የጋስ ልዩነትን የሚያሳይ ከታች ያለውን ሠንጠረዥ በክፈል ውሰጥ እንዲወያዩበት አድርጉ፡፡

| ጠጣር | ፈሳሽ | ጋስ |
|---|---|---|
| ውስን ቅርጽ አለው | ውስን ቅርጽ የለውም | ውስን ቅርጽ የለውም |
| አይታመቅም | አይታመቅም | ይታመቃል |
| ትልቅ እፍጋት አለው | ከጠጣር ያነሰ እፍጋት አለው | አነስተኛ እፍጋት አለው |
| በቀላሉ አይሰራጩም | በቀላሉ ይሰራጫሉ | በቀላሉ ይሰራጫሉ |

**የጠጣር፣ የፈሳሽና የጋስ የሁነት ለውጥ**

አንድ ዓይነት ቁስ አካል በተለያየ ሁነት መገኘቱ የፊዝካል ለውጥ መሆኑን አስገንዝቡኣቸው፡፡ ይህን ሀሳብ ለማስገንዘብ በሶስቱም ሁነት የሚገኘውን ውሃ ተማሪዎች እንዲገልፁ እድል ከሰጣሀቸው በኋላ በረዶ ሲሆን በጠጣር ሁነት መገኘቱን ሲቀልጥ በፈሳሽ ሁነት መገኘቱንና ሲተን ደግሞ በጋስ ሁነት መሆኑን አስገንዝቡ፡፡

የመጠነ አካል ለውጥ ፊዚካላዊ ለውጥ መሆኑን አስገንዝቡ ለምሳሌ ውሃ በበረዶ ( ጠጣር) በፈሳሽና በትነት(ጋስ) መልክ ይገኛል፡፡ ጋስ ከጠጣርና ከፈሳሽ

የሚለይበት ባህርይ አንዱ የመታመቅ ችሎታና መስፋፋት (መሰረጨት) መሆኑን አስገንዝቡ፡፡

የጋስ በቀላሉ የመታመቅ ችሎታን ለማስገንዘብ ፊኛ በንፋስ ሞልታችዉ መታመቅ መቻሉን አሳዩ፡፡ በተጨማሪም ንፁህ ስሪንጅ በመውሰድ ወደ ኋላ ሳቡ ከሳባችሁ በኋላ የጫፉን ቀዳዳ በመድፈን ስሪንጁን ከኋላ ወደ ታች መግፋት፡፡ ለምን እነደማይገፋ በመጠየቅ ጋስ ቦታ በመያዝ መክንያት መሆኑን ይገለፅላቸው፡፡ መጀመሪያ ሲንቀሳቀስም የጋሶች ሞሎኪዩሎች ተረርቀው ስለሚገኙና በሚትገፉት ጊዜ ስለሚታመቅ መሆኑን አስገንዝቡ፡፡

ቁስ አካል ሁነቱን የሚቀያይር መሆኑን አስገንዝቡ፡ ይህን ለውጥ ለማካሄድ ምን እንደሚያስፈልግ ጠይቁ፡፡

የዚህ የሁናቱ ለውጥ የፊዝካላዊ ለውጥ መሆኑን አስገንዝቡ፡፡

ጠዋት የሚታየው ጤዛ ፀሐይ በምትወጣበት ጊዜ የሚጠፋበት ምክንያት ጤዛ ፈሰሽ ውሃ መሆኑን፤ የሙቀት ጉልበት ሲያገኝ ወደ ትነት ውሃ የሚለወጥ መሆኑን አስገንዝቡ፡፡

የቁስ አካል የሁነት ለውጥን ለማስረዳት ያዘጋጁትን ስዕል ለተማሪ በማሳየት የሙቀት ጉልበት ሲያገኝ ሁነት መቀየር መቻሉን አስገንዝቡ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንዲኖራቸው ማገዝ**

ልዩ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማፍራት ተማሪዎችን ማነቀቃትና ስለ ጠጣር፣ ፈሰሽና ጋስ ቀላል ያለ ሙከራ ሰርተው ክፍል ውስጥ እንዲያሳዩ በማበረታታት ሙከራ የሚያቀርቡትን ተማሪዎች ማድነቅ አስፈላጊ ነው፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- በአካባቢያቸው የሚገኑ ነገሮችን በሶስቱ ሁነት መመደብ መቻላቸውን ጥያቄ በመጠየቅ ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

- የጠጣር የፈሳሽና የጋስን ባህሪያትን በቡድን በመሆን ሙከራ ሰርተው ለክፍል ገለፃ እንዲያደርጉ ማድረግ፡፡
- የሙቀት ጉልበት ሲጨምር ነገሮች ወዴት መቀየር እንደሚችሉ በምሳሌ በመታገዝ እንዲገልፁ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች በጠጣር በፈሳሽና በጋስ መካከል በለው ልዩነት ላይ እንዲወያዩ በማድረግ በቡድን በመመደብ የተረዱትን እንዲገልጹ በማድረግ መመዘን ይቻላል፡፡

## የተግባራት መልስ

### ተግባር 1.5

| ጠጣር | ፈሳሽ | ጋስ |
|---|---|---|
| አፈር | ውሃ | ንፋስ |
| ድንጋይ | ዘይት | የውሃ ትነት |

### ተግባር 1.6

| ጠጣር | ፈሳሽ | ጋስ |
|---|---|---|
| መኪና | ውሃ | የፋብሪካ ጪስ |
| ድንጋይ | ቡና | የውሃ ትነት |
| ላፐቶፐ | | ንፋስ |
| ፋስ | | |

### ተግባር 1.7

1. ጠመኔ ነጭ ቀለም ሲኖረው፤ ጥቁር ደንጋይ ጥቁር ቀለም አለው፡፡
2. ከሁለቱ ጥቁር ድንጋይ በጣም ይጠነክራል፡፡

3. ውሃ ወደ ብርጭቆ አይገባም፡፡
4. ውሃ ወደ ብርጭቆ መግባት የማይችለው ምክንያት አየር/ንፋስ ብርጭቆ ውስጥ ቦታ ስለያዘ ነው፡፡

**ተግባር 1.8**

ውሃ በማንቆርቆሪያ እሳት ላይ ሲጣድ ፈሰሽ ውሃ ወደ ትነት ይለወጣል፡፡ ይህ ለውጥ ከፈሳሽ ሁነት ወደ ጋስ ሁነት መቀየሩን ያሳል፡፡

## 1.5 የብርሃን ጥቅም

ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት--------------------- 3

***የምዕራፉ ትምህርት የመማር ውጤቶች***

በዚህ በምዕራፉ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡-

- የብርሃን ጥቅሞችን ይዘረዝራሉ፡፡

***ዋና ዋና ሀሳቦች***

ብርሃን ከጉልበት ዓይነቶቸ ውስጥ አንዱ ሆኖ ሕይወት ላላቸው ሁሉ አስፈላጊ ነው፡፡ በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች ለመለየት ብርሃን መኖር አለበት፡፡ ዕፅዋት ምግባቸውን ለማዘጋጀትና ለማደግ ብርሃን ያስፈልጋቸዋል፡፡ የብርሃን ምንጭ ብርሃንን የሚያመነጭ አካል ሲሆን፤ እነርሱም በሁለት ቦታ ይከፈላሉ፡፡ እነሱም የተፈጥሮ የብርሃን ምንጭና ሰው ሰራሽ ናቸው፡፡ በዚህ ርዕስ ስር ተማሪዎች ብርሃን ምን ጥቅም እንዳለው ይማራሉ፡፡ እንዲሁም የብርሃን ምንጮችን ይማራሉ፡፡

ይህን ርዕስ ለማስተማር ከመማር ማስተማር ዘዴዎች ውስጥ የቡድንና የጥንድ ውይይት፣ ገለጻና የክፍል ስራን በመስጠት ማካሄድ ይቻላል፡፡

**ቅደመ ዝግጅት**

የዚህ ትምህርት ርዕስ ከመጀመሩ በፊት በቂ ዝግጅት ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ትምህርት ክፈለ ጊዜ የትምህርት ዕቅድ በጥልቀት ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ የብርሃን ጥቅም የሚለውን ርዕስ ለማስተማር መምህራን ቀድመው ራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ ይህን ለማድረግ ከርዕሱ ጋር ተያያዥ መረጃ ከተማሪዎች መፅሃፍና ከአጋዥ መፅሐፍት በማንበብ መዘጋጀት ወሳኝ ነው፡፡ ይህን ርዕስ ለማስተማር ከብርሃን ጥቅሞችና ምንጮች ጋር የሚሄድ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ከአካባቢ ከሚገኙ ነገሮቸ በማዘጋጀት መጠቀም ነው፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

ማስተማር ከመጀመሩ በፊት መምህራን አስፈላጊ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ሁሉም ዝግጅት ካለቀ በኋላ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎችን ማነቀቃት፤ በመቀጠል ተማሪዎች የብርሃን ጥቅምና ምንጮች እንዲዘረዝሩና ውይይት በማድረግ የቤት ስራ እንዲሰሩ መስጠት፡፡ ሰርተው ያመጡትን የቤት ስራ በመመልከት ትክክለኛ መልስ ከሆነ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ መልሱ ትክክል ካልሆነ ደግሞ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ አስፈላጊውን ገለፃ መስጠት ነው፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንዲኖራቸው ማበረታታት**

የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ ለማዳበር በአካከበቢያቸው በሚገኙ ነገሮች የብርሃን ምንጮችን ሞዴል እንዲያዘጋጁ ማበረታታትና ላዘጋጁት ተማሪዎች የማበረታቻ ሞራል መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ተማሪዎቹ የብርሃንን ጥቅም በሚዘረዝሩበት ወቅት ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅ የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ተጨማሪ ሌሎች ተግባራትን ለተማሪዎች በመስጠት ስራቸውን በመከታተል ግብረ መልስ መስጠት፡፡
- ተማሪዎቹ ተጨባጭ ተግባራትን በሚሰሩበት ወቅት አቅጣጫ በማሳየት ድጋፍ ማድረግ፡፡
- የተማሪዎችን ሁኔታ በየጊዜው እየመዘገቡ መሄድ፡፡
- በየጊዜው ለተማሪዎች ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**የምዕራፍ 1 መልመጃ መልስ**

**የእውነት ሐሰት ጥያቄዎች**

1. እውነት 2. ሐሰት 3. እውነት 4. ሐሰት 5. እውነት
6. ሐሰት 7. እውነት 8. እውነት 9. እዉነት 10. እውነት
11. እውነት 12. እውነት 13. ሐሰት 14. ሐሰት

**የአዛምድ ጥያቄዎች**

1. ለ 2. ሀ 3. መ 4. ሠ 5. ሐ

**የምርጫ ጥያቄዎች**

1. መ 2. ሀ 3. ሐ 4. መ 5. ሀ
6. ለ 7. ሀ 8. መ 9.ሀ 10. ለ

# ምዕራፍ 2: መገኛ

ለምዕራፉ ትምህርተ የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ………………….....34

ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ውጤቶች

- የአቅጣጫ ምንነት ይገልፃሉ፤
- አራቱን አቅጣጫዎች ይለያሉ፤
- አቅጣጫዎችን በመጠቀም የአንድ ቦታ መገኛ ይናገራሉ፤
- የአንድ ቦታ መገኛ የሚገለፅበት ዘዴ ይረዳሉ፤
- አንጻራዊና ፍፁማዊ መገኛን ይለያሉ፤
- የዞናቸውን አንጻራዊ መገኛ ይረዳሉ፤
- የኬክሮስና የኬንትሮስ መስመሮችን በመጠቀም የዞናቸውን መገኛ ይለያሉ፤
- ጎረቤት የሆኑ ዞኖችን ስም ይዘረዝራሉ።

**መግቢያ**

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች የዞናቸውን ፍጹማዊና አንጻራዊ መገኛ፤ በዞናቸው የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችና የአዋሳኝ ዞኖች መገኛ ይማራሉ ።

## 2.1 የዞናችን መገኛ

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት …………………….5

ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገቡ የመማር ውጤቶች፡

- የመገኛን ምንነት ያብራራሉ፤
- አራቱን ዋና ዋና አቅጣጫዎችን ይለያሉ፤
- የአራቱን ዋና ዋና አቅጣጫዎች ጥቅም ይረዳሉ።

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በዚህ የትምህርት ይዘት ሥር ተማሪዎች ስለመገኛ ምንነት፤ የአራቱ አቅጣጫዎችና ጥቅማቸውን ለይተው ይማራሉ፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

- አለታዊ ዕቅድ ማዘጋጀት
- የማጣቀሻ መጻሐፍትን በማንበብ የአቅጣጫዎችን ጥቅም ግንዛቤ ማዳበር፡፡
- አቅጣጫዎችን ለማስተማር ተማሪዎችን ከክፍል ውጭ ፊታቸውን ወደ ፀሀይ መውጫ በማድረግ ጀርባቸው ፤ ቀኝና ግራ እጃቸው የሚያሳዩትን አቅጣጫዎች እንድለዩ ማድርግ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ፡-**

ይህንን የትምህርት ይዘት ለማስተማር የተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ትችላላችሁ ፡፡ ነገር ግን ከትምህርቱ ይዘት ጋር ይበልጥ አብሮ የሚሄድ ከሚከተሉት የመማር ማስተማር ዘዴ ውስጥ መምረጥ አስፈላግ ነው፡፡ እነሱም የቡድን ሥራ፤ ሠርቶ ማሳያ፤ ጥያቄና መልስ የመሳሰሉትን መጠቀም ትችላላችሁ፡፡

በዚህ የትምህርት ይዘት ዋና ትኩረት መሆን ያለበት ተማሪዎች የዞናቸውን መገኛ በጥያቄና መልስ በመታገዝ እንዲያብራሩ አድርጉ፡፡ ተማሪዎች የሚሰጡትን መልስ በጥቁር ሠሌዳ ላይ ከፃፋችዉ በኃላ የትኛው ትክክል እንደሆነና እንዳልሆነ ከተማሪዎች ጋር ለዩት ፡፡ ተማሪዎች የሚኖሩበትን ወረዳ ጨምሮ ስንት ወረዳዎቸ በዞናቸው ውስጥ እንዳሉ እንድናገሩ ማድረግ ነዉ፡፡

ተማሪዎች ዞን ማለት የተለያዩ ወረዳዎችን በስሩ ያቀፈ የአስተዳደር አካል መሆኑን ከተረዱ በኃላ አቅጣጫን በማስመልከት ግንዛቤያቸውን ለመገምገም በጥያቄና መልስ ዘዴ እንድገልጹ ዕድል ስጧቸው ፡፡
በተጨማሪም ተማሪዎች የሚኖሩበት ወረዳና ሌሎች በዞናቸው ውስጥ የሚገኙ የወረዳዎችን ስም እንድዘረዝሩ ዕድል ስጧቸው፡፡ ወረዳቸውን የሚያዋስኑ ወረዳዎች ስም ዝርዝር  እንድያቢራሩ ማገዝ ተገቢ ነው፡:
ተማሪዎች አራቱን ዋና ዋና አቅጣጫዎችን በትክክል እንዲረዱ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ በስዕል 1፡1 የተብራሩትን ሀሳቦችን በሙሉ ማስጨበጥ አለባችሁ፡፡ ተማሪዎች አራቱን  ዋና ዋና አቅጣጫዎች (ሰሜን ፤ ደቡብ ፤ ምዕራብና ምስራቅ) በተግባር ሥራ እንዲያሳዩ ማድረግ፡፡
ተማሪዎች ወደ ፀሀይ መውጫ አቅጣጫ ምሥራቅ ላይ ፊታቸውን አዙረው ጀርባቸው፤ ቀኝና ግራ እጃቸው የሚያመለክቱትን አቅጣጫዎችን እንዲያብራሩ አድርጉ፡፡ ተማሪዎች ይህንን የተግባር ሥራ ሲሰሩ በተማሪዎች መጽሐፍ ስዕል 1፡1 ላይ የተጠቀሱትን ሀሳቦች መሰረት በማድረግ እንዲሰሩ ማገዝ አለባችሁ፡፡ እንደዚሁም ፀሀይ በምስራቅ ወጥታ በምዕራብ አቅጣጫ አንደምትጠልቅ እንድገናዘቡ አድርጉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ሰሜንና ደቡብ አቅጣጫዎችን ስለመለየታቸውን እርግጠኛ ለመሆን በቡድንና በግል ፊታቸውን ወደ ፀሀይ መውጫ አዙረው አራቱን አቅጣጫዎችን እንዲናገሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው ፡፡
ከተግባር ስራ መልስ ወደ ክፍል ሲመለሱ ካርታን በመጠቀም አራቱን ዋና ዋና አቅጣጫዎችን  ምሥራቅ ፤ምዕራብ ፤ሰሜንና ደቡብ  በትክክል ማወቃቸውን ለመረዳት በግልና በቡድን እንዲያብራሩ ዕድል ስጧቸው  ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማገዝ**

ተማሪዎች በራሳቸው አካሄድ የአንድ ሀገር ወይም ቦታ መገኛ እንድያብራሩ ማበረታታት አለባችሁ፡፡ በትምህርት ይዘት ውስጥ አቅጣጫን ለመለየት ከተቀመጡት ዘዴዎች ሌላ ካሉ ወይም በአካባቢያቸው የሚጠቀሙበት ስልቶችን እንዲያብራሩ ዕድል ስጧቸው ፡፡ በመጨረሻም ከትምህርቱ ይዘት ጋር በማቀናጀትና በማስተሳሰር አቅርቡላቸው ፡፡ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያሉትን ግንዛቤዎች ከትምህርታቸው ጋር ማቀናጀት የፈጠራ ችሎታቸው እየተጠናከረ ስለሚሄድ ነው፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ተማሪዎች አቅጣጫዎችን ለመለየት በተግባር ስራ ስለማመዱ የቆዩትን በትክክል መረዳታቸውን ለመገምገም በክፍል ውስጥ የፅሁፍና የቃል ጥያቄዎች ይዘጋጅላቸው፡፡
- ተማሪዎች በቡድንና በግል ሠርተው ሲያሳዩ ያልገባቸው ካለ በቂ እገዛ ይደረግላቸው፡፡
- ተማሪዎች በተግባር ሥራ ላይ ያሳዩትን የግንዛቤና የክህሎት ለውጥ በየቀኑ መመዝገብ አለበት፡፡
- የተግባር ሥራ በሚያከናውኑ ጊዜ የሚያስቸግራቸውን እገዛና ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

አቅጣጫዎች የአንድ ሀገር ወይም ቦታ መገኛ የት እንደሆነ ያሳያል፡፡ ሰዎች በየቀኑ ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከየት ወዴት የሚሉ አቅጣጫዎች፤ የቆዩበትና የሄዱበት ቦታ ልዩነት ሊነጋገሩበት ይችላሉ፡ ፡ እርስ በራሳቸው የሚያደርጉትን ውይይት ለመገንዘብና ከተለያዩ ቦታዎች

የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በአቅጣጫዎች በመታገስ የቦታዎች መገኛ ይገልጻሉ፡፡

**የተግባር 2፡1መልሶች**

1. ቦና ከአብዲ በስተሰሜን አቅጣጫ ይገኛል
2. አብዲ ከቦና በስተደቡብ አቅጣጫ ይገኛል
3. ጫልቱ ከደራርቱ በስተምዕራብ አቅጣጫ ትገኛለች
4. ደራርቱ ከጫልቱ በስተምስራቅ አቅጣጫ ትገኛለች

## 2.2 የአንጻራዊ መገኛ ምንነት

የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ……..5

ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃት

- የቦታዎች አንጻራዊ መገኛ ያብራራሉ
- የዞናቸው አንጻራዊ መገኛ ያውቃሉ

**ዋና ዋና ነጥቦች**

የዚህ ትምህርት ይዘት ፍሬ ሀሳብ የአንጻራዊ መገኛ ምንነት ነው፡፡ አንጻራዊ መገኛ በተለያዩ መንገድ ይገለጻል፡፡

አንድ ቋሚ የሆኑ ነገሮችን መጠቀም እንችላለን፡፡ ለምሣሌ ተራራዎች፤ ትላልቅ ወንዞች፤ ፖርኮችና የመሳሰሉትን በመጠቀም የአንድ ቦታ አንጻራዊ መገኛ መግለፅ ይቻላል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት፤
- አቅጣጫዎችን የሚያመለክቱ የተለያዩ መፅሐፍትን ማንበብ
- ሁሉንም ዞኖች በውስጡ ያቀፈ የኦሮሚያ ካርታን መጠቀም፤

- የኦሮሚያ ካርታ ላይ ሁሉንም ዞኖች የተለያዩ ቀለሞችን በመቀባት መጠቀም፤
- አንጻራዊ መገኛ ለማስተማር ከክፍል ውጭ የተግባር ስራ ለማሰራት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

የመማር ማስተማር ዘዴዎች ብዙ ናቸው ፡፡ እነሱም ተማሪዎችን በቡድን ማወያየት፤ ሠርቶ ማሳያ፤ በጥያቄና መልስ አማካኝነት ማስተማር ይቻላል፡፡ ነገር ግን ከትምህርት ይዘቱ ጋር ተያያዥነት ያለውና በቀላሉ የተማሪዎችን ግንዛቤ ማበልፀግ የሚችል ዘዴዎችን በመምረጥ የመማር ማስተማር ዘዴን ማካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡

መገኛ በሁለት መንገዶች እንደሚገለፅ ለተማሪዎች ማስረዳት አለባችሁ፡፡ እነሱም አንጻራዊና ፍጹማዊ መገኛ መሆኑን ማስረዳት፡፡ የተለያዩ ቋሚ የሆኑ ነገሮችን እንደ መነሻ ቦታ በመውሰድ በአንጻራዊ ዘዴ የቦታዎች መገኛ መለየት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ ወረዳ፤ ዞን፤ ክልል፤ ሀገርና የተለያዩ የመልከዓ ምድር ዓይነቶችን ተራራ፤ ሸለቆ፤ ወንዞችና የመሳሰሉትን በመጠቀም አንጻራዊ መገኛን መግለፅ እንችላለን፡፡

ተማሪዎች ይህንን ሀሳብ በትክክል መረዳታቸውን ለመገምገም በአካባቢያቸው የሚገኙትን ታዋቂ ቦታዎች ከዘረዘሩ በኃላ አንዱን በመውሰድ ከሌሎች ቦታዎች ጋር በምን አቅጣጫ ላይ እንደሚገኙ እንዲያብራሩ አድርጉ ፡፡ ይህንን የተግባር ስራ ከሰሩ በኃላ በክፍል ውስጥ ስዕል በመሣል በመሬት ላይ በተጨባጭ የሚገኙ የቦታዎችን አንጻራዊ መገኛ እንድገልፁ አድርጉ፡፡

ተማሪዎች የኦሮሚያ ካርታን በመጠቀም የሚኖሩበትን ዞን ከሌሎች ዞኖች ጋር በምን አቅጣጫ ላይ እንደሚገኝ በአንጻራዊ ዘዴ እንዲገልጹ አድርጉ ፡፡ እንድሁም አዋሳኝ የሆኑ ዞኖችን አንድ በአንድ እንድዘረዝሩ አበረታቱ፡፡

ይህንን የተግባር ስራና በአሳታፊ ዘዴ ካስተማራችሁ የተማሪዎች ግንዛቤ እየዳበረ የሚሄድ መሆኑን ከግምት በማስገባት እገዛ ማድርግ አለበችሁ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንድያዳብሩ ማበረታታት**

ተማሪዎች በራሳቸው ፈጠራ ችሎታ የአንድን አካባቢ መገኛ በአንጻራዊ ዘዴ እንዲያሳዩ ማበረታታትና መደገፍ አለባችሁ፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- የአንጻራዊ መገኛ ምንነት ተማሪዎች ትክክለኛ ግንዛቤ መጨበጣቸውን መከታተል
- ተማሪዎች በዚህ የትምህርት ይዘት ውስጥ የተከታተሉትን የተግባር ስራዎችን በቡድንና በግል እንዲሰሩ ማበረታታት
- የተማሪዎች ባህሪይና ግንዛቤ ለውጥ የሚያሳይ በእለታዊ መዝገብ ላይ በተከታታይ መመዝገብ
- ተማሪዎች በየእለቱ በሚያሳዩት የግንዛቤ ለውጥ በማመዛዘን አዎንታዊ ወይም ገንቢ ግብረ መልስ መሰጠት፡፡

## 2.3 ፍጹማዊ መገኛ ምንነት

ለትምህርቱ የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ……..5

**ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃት**

- የፍፁማዊ መገኛ ምንነት ያብራራሉ፤
- የኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮችን በመጠቀም ፍጹማዊ መገኛ ይለያሉ፤
- የኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች ምንነት ይለያሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

- በዚህ ርእስ ውስጥ ዋና ዋና ነጥቦች የአንጻራዊና ፍጹማዊ መገኛ፤ ኬንትሮስና የኬክሮስ መስመሮች ናቸው፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

- ዕለታዊ ዕቅድ ማዘጋጀት
- የተማሪዎች መማሪያ መፅሐፍና ሌሎች መፅሐፍትን ማንበብ

በኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች የተቀናጀ ካርታን በመጠቀም በተማሪ መፅሐፍ በስዕል 1.4፤ 1.5 ና 1.6 ላይ የተቀመጡትን ማብራራት፡፡ የኦሮሚያ ክልል ካርታን በመጠቀም በኬክሮስና በኬንትሮስ መስሮች አማካኝነት የዞናቸውን ፈጹማዊ መገኛ እንዲያውቁ ማድረግ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**


የመማር ማስተማር ዘዴ ከትምህርት ይዘቱ ጋር ይበልጥ አብሮ የሚሄድ መለየትና መምረጥ አለባችሁ፡፡ ከተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ለትምህርቱ ይዘት ምቹ የሆነውን ጥያቄና መልስ፤ የቡድን ውይይት ወይም የክፍል ስራና ሠርቶ ማሳያ ውስጥ በመምረጥ መጠቀም ፡፡

የኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች ምንነት ለማስረዳት በተማሪ መጽሐፍ ላይ በስዕል 1፡6 የተሰጠውን መሰረት በማድረግ በጥቁር ሠላዳ ላይ ስዕል በመሳል በትክክል ስለመረዳታቸውን መከታተል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በተግባር ስራ በቡድን ወይም በግል ሠርቶ እንዲያሳዩ ማድረግ፤ በመጨረሻም የፍጹማዊ መገኛ ምንነት በትክክል ማስረዳት፡፡

ፍጹማዊ መገኛ የአንድን ቦታ ትክክለኛ መገኛውን በዲግሪና አቅጣጫ የሚያመላክት መሆኑን ማስረዳት፡፡ በኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች የተቀናጀ ካርታ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የኬክሮስና ኬንትሮስ

መስመሮች የሚያመለክት በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን መጠቀም ተገቢ ይሆናል፡፡

የኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች በመጠቀም የቦታዎችን መገኛ በዲግሪና አቅጣጫ ለመለየት የሚያግዝ የሚከተለውን ስዕል መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡




ሥዕል 2፤1 የኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች

በሥዕሉ ላይ እንደሚትመለከቱት የሀ ፊደል በ20 ዲግሪ ሰሜንና በ40 ዲግሪ ምስራቅ አቅጣጫ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ማለት የሀ ፊደል ከምድር ወገብ በ20 ዲግሪ ሰሜን ርቀት ላይና ከትልቁ ሜሪዲያን ደግሞ በ40 ዲግሪ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ላይ እንደሚገኝ ማስረዳት፡፡ የኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮችን

ተጠቅመን የአንድን ቦታ መገኛ ስንገልፅ መጀመሪያ መገለፅ ያለበት የኬክሮስ መስመር ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ የኬንትሮስ መስመር ነው፡፡

በዚህ መልኩ የ ለ መገኛ አቅጣጫ በዲግሪ ስንት ላይ እንደሚገኝ ተማሪዎችን በተግባር ስራ እንዲለማመዱ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በስዕሉ ላይ እንደሚትመለከቱት በ20 ዲግሪ በስተደቡብ አቅጣጫና በ40 ዲግሪ ምዕራብ አቅጣጫ ላይ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የዞናችንና የወረዳችን መገኛ በኬክሮስና በኬንትሮስ መስመሮች በመታገዝ ትክክለኛ መገኛቸውን መለየት አስፈላጊ ነው፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ መደገፍ**

ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸው እንዲዳብሩ በአሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴ ማበረታታትና መደገፍ አስፈላጊ ነው፡፡ ኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች በመጠቀም የቦታዎች መገኛ በራሳቸው አካሄድ እንዲያብራሩ ለተማሪዎች ዕድል ይሰጣቸው፡፡ በተግባር ስራ ሙሉ ግንዛቤ እንድያገኙና የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ አስፈላጊ እገዛ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

የፍጹማዊ መገኛ ምንነት መረዳታቸውን ለመገምገም የግንዛቤና ያሳዩትን የባህሪይ ለውጥ መከታተል ተገቢ ነው፡፡

ተማሪዎች በቡድንና በግል በዚህ የትምህርት ይዘት ውስጥ የሚገኙ ተግባራትና መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ የተማሪዎችን ግንዛቤና የሚያሳዩትን የባህሪይ ለውጥ በእለታዊ መዝገብ ላይ በተከታታይ መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች በሚሰሩት የተግባር ስራዎችና በግል በሚሰሩት ስራ ገንቢ አስተያየት መስጠት፡፡

# 2.4 የዞናችን አንጻራዊ መገኛ

ለዚህ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት………………………..…...4

ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱባቸዉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

- የዞናቸውን አንጻራዊ መገኛ ይለያሉ፤
- የዞናቸውንና አዋሳኝ ዞኖች አንጻራዊ መገኛ ይለያሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በዚህ የትምህርት ይዘት የዞናቸውን አንጻራዊ መገኛ አቅጣጫዎችን በመጠቀም የሚያዋስናቸውን የዞኖች ወይም ወረዳዎች ስም ይዘረዝራሉ፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

- ዕለታዊ የትምህርት እቅድ ማዘጋጀት፤
- በአንጻራዊ መገኛ ዙሪያ ግንዛቤ ለማዳበር የተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍና ሌሎች መጽሐፍትን ማንበብ፤
- የኦሮሚያ ክልል ካርታ ላይ በኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች በመጠቀም የዞናቸውን መገኛ መለየት፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

ይህንን የትምህርት ይዘት ለማስተማር የተለያየ የመማር ማስተማር ዘዴ፤ በቡድን ስራ፤ ሠርቶ ማሳያ፤ ጥያቄና መልስ ውስጥ ምቹ የሆነውን በመምረጥ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች አራቱን አቅጣጫ በመጠቀም የዞናቸውን አንጻራዊ መገኛን በተግባር ስራ እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

በተማሪዎች መጽሐፍ ውስጥ የምስራቅ ሸዋ ዞን አንጻራዊ መገኛ እንደ ምሳሌ በመውሰድ ዞናቸው ከሌሎች ዞኖች በምን አቅጣጫ ላይ እንደሚገኝ በተግባር ስራ እንዲለዩ ማድረግ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እነዲያዳብሩ መደገፍ**

የተማሪዎች ፈጠራ ችሎታ እንዲዳብር አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የዞናቸውን አንጻራዊ መገኛ አቅጣጫዎችን በመጠቀም እንዲናገሩ እድል ሰጧቸው ፡፡

**1. ተከታታይ ምዘና**

በተማሪዎች መጽሐፍ ውሰጥ በተቀመጠው መሠረት የዞናቸውን አንጻራዊ መገኛ አቅጣጫዎችን በመጠቀም ከተግባር ስራዎች በኃላ በትክክል እንድገልጹ መከታተል አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች በቡድንና በግል በዚህ የትምህርት ይዘት ውስጥ ያሉትን የተግባር ስራዎችና መልመጃዎችን በትክክል መስራታቸውን መከታተል፡፡

ተማሪዎች በየቀኑ የሚያሳዩትን የባህሪይ ለውጥና ግንዛቤ በእለታዊ መዝገብ ላይ ማስፈር ተገቢ ነው፡፡ ተማሪዎች በተግባር ስራና መልመጃዎችን ሲያከናውኑ ግብረ መልስ መስጠትም አስፈላጊ ነው ፡፡

**የተግባር 2.2 መልስ**

ተማሪዎች ይህንን የተግባር ስራ በቡድን እንዲሰሩ የተገደበ ጊዜ /ሰዓት / ይሰጣቸው፡፡ ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ በተግባር ስራ ላይ ከተወያዩ በኃላ በኦሮሚያ ካርታ ላይ የዞናቸውን መገኛ የት እንደሆነና ዞናቸውን የሚያዋስኑ የጎረቤት ዞኖች መገኛ አቅጣጫ እንዲለዩ አድርጉ ፡፡

በመጨረሻም የዞናቸውን መልካ ምድር ምን ዓይነት ቅርጽ እንዳለው መገመት እንዲችሉ በኦሮሚያ ካርታ ላይ ዞናቸውን በትክክል አሳዩአቸው፡፡ የዞናቸውን ካርታ ሰርቶ እንዲያቀርቡ የቤት ስራ ይሰጣቸው፡፡

## 1.5 የዞናችን ፍጹማዊ መገኛ

ለዚህ ትምህርት የተሰጠ የክፍል ጊዜ ብዛት ……………………….……4

ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱባቸዉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

- የዞናቸውን ፍጹማዊ መገኛ ይለያሉ፤
- በካርታ ላይ የዞናቸውን ፍጻማዊ መገኛ ያሳያሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥበች**

በዚህ የትምህርት ይዘት ውስጥ ተማሪዎች የዞናቸውን ፍጹማዊ መገኛ በኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች በመጠቀም ትክክለኛ የአቅጣጫ መገኛና በስንት ዲግሪ ላይ እንደሚገኙ ይማራሉ፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

- ዕለታዊ የትምህርት እቅድ ማዘጋጀት
- የማጣቀሻ መጽሐፍትን ማንበብ
- በኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች ቅንጅት የተሰራ የኦሮሚያ ክልል ካርታን መጠቀም

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

ይህንን ትምህርት ይዘት ለማስተማር ምቹ የሆነውን የመማር ማስተማር ዘዴን፤ የቡድን ስራ፤ በጥያቄና መልስና ከመሳሰሉት ውስጥ በመምረጥ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

የዞናችን ፍጻማዊ መገኛ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ በኬንትሮስና በኬክሮስ መስመሮች ቅንጅት የተሰራ የኦሮሚያ ካርታ ለመማሪያነት በመጠቀም ተማሪዎች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ መደገፍ**

የፈጠራ ችሎታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎችን ለማግኘት የዞናቸውን ፍጹማዊ መገኛ በራሳቸው አካሄድ እንዲያብራሩ እድል ስጣቸው፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

በኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች ቅንጅት የተሰሩ ካርታ በመጠቀም ዞናቸው በስንት ዲግሪና በየትኛው አቅጣጫ እንደሚገኝ ማወቃቸውን መገምገም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በጥቁር ሰሌዳ ላይ የኦሮሚያን ካርታ ሠርቶ የዞናቸውን መገኛ ተማሪዎች እንዲያሳዩ ማድረግ ፡፡

- ተማሪዎች በዚህ የትምህርት ይዘት ውስጥ ያሉትን የተግባር ስራዎችና መልመጃዎችን በቡድንና በግል እንዲሰሩ ማድረግና አስፈላጊ እገዛ መስጠት፡፡
- ተማሪዎች በየቀኑ የሚያሳዩትን የባህርይ ለውጥና ግንዛቤ በእለታዊ መዝገብ ላይ ማስፈር
- ተማሪዎች የተግባር ስራዎችን ሲሰሩ ገንቢ የሆኑ ግብረ መልስ መስጠት

## 2.6 በዞኖችን የሚገኙ ታወቂ ቦታዎች መገኛ

ለዚህ ትምህርት የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት ……………..2

ተማሪዎ ቢያንስ ልደርሱባቸዉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

- በዞናቸው የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎች ስም ይዘረዝራሉ፤
- በዞናቸው የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎች መገኛ ያሳያሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በዚህ ርእስ ስር ዋና ዋና ነጥቦች በዞናችን የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎች በዝርዝር ስለሚማሩ ተማሪዎች እነዚህን ታዋቂ ቦታዎች ለይቶ ማወቅ ይገባቸዋል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

- እለታዊ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት፤
- የማጣቀሻ መጽሐፍትን ማንበብ፤
- በዞኑ ውስጥ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችን ስምና መገኛቸውን መለየት ፡፡

ከተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ጥያቄና መልስ፣ የቡድን ስራ፣ ሠርቶ ማሳያ ውስጥ ከርዕሱ ጋር የሚስማማዉን መምረጥ አስፈላጊ ነው፡፡

በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ብዙ ታዋቂ የሆኑ ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ በዚሁ መሠረት በዞናቸው ታዋቂ የሆኑ የቦታዎች ስም ዝርዝርና መገኛቸውን እንዲያውቁ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የታዋቂ ቦታዎች መገኛ አቅጣጫዎችን በመጠቀም የት እንደሚገኙ እንዲያብራሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለዉ ስዕል 1.1 ላይ የተቀመጠውን እንደ ምሳሌ በመውሰድ በዞናቸው ውስጥ የሚገኙ ወረዳዎች ስም እንዲዘረዝሩ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ መደገፍ**

የተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንዲያዳብሩ አሳተፊ የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴና በውስጣቸው ያለውን ተሰጥዖ እንዲያንጸባርቁ ማድረግ፡፡ ተማሪዎች በጉብኝት መልክ በዞናቸሁ ከሚገኙ የታዋቂ ቦታዎች በቅርበት የሚገኝ አንድን በአካል ጉብኝት እንዲያደርጉ ማድረግ፡፡ ከጉብኝት በኃላ ያዩትን በሪፖርት አቀናጅተው እንዲያቀርቡ በማድረግ ለሰሩት ስራ ውጤት ይያዝላቸው፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- በርዕሱ ውስጥ የተማሩትን ጭብጥ ሀሳቦች በበቂ ሁኔታ ያልተገናዘቡ ከሆነ አስፈላጊ እገዛ ይደረግላቸው፡፡

- ተማሪዎች በትምህርት ይዘት ስር የሚገኙ የተግባር ስራና መልመጃዎችን በቡድንና በግል ሲሰሩ ተከታታይ ክትትል በማድረግ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ማገዝ አስፈላጊ ይሆናል፡፡
- የተማሪዎች ተከታታይ የባህርይ ለውጥና ግንዛቤ በዕለታዊ መዝገብ ላይ ማስፈር፡፡
- በተግባር ስራና በግል ተማሪዎች የሚያከናውኑትን በመገምገም ገንቢ አስተያት መስጠት ፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

**ተግባር 2፡3**

ተማሪዎች በዞኑ ውስጥ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችን ተራ በተራ ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በክፍል ያቀረቡትን ሪፖርት በመገምገም እርማት ይሰጥበት፡፡

## 2.7 የአዋሳኝ ዞኖች ስም እና መገኛ

ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸው የመማር ብቃት ፡-

- አዋሳኝ የሆኑ ዞኖች ስም ይዘረዝራሉ፤
- የዞናቸውን አንጻራዊ መገኛ ይገልጻሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በዚህ ትምህርት ይዘት ስር ዋና ዋና ነጥቦች የዞናቸውን አንጻራዊ መገኛና አዋሳኝ የሆኑ ዞኖች ስም ዝርዝር ላይ ያተኩራል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት

- የኦሮሚያ ክልል ካርታ ዞኖችንና የከተማ አስተዳደር የያዘውን በማዘጋጀት መጠቀም

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

ከትምህርት ይዘቱ ጋር ይበልጥ አብሮ የሚሄድ የመማር ማስተማር በቅድሚያ መለየት አስፈላጊ ነው፡፡ ከተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ለምሳሌ ጥያቄና መልስ፤ የቡድን ስራን በመጠቀም ማስተማርና ሠርቶ ማሳያ ውስጥ ከትምህርቱ ይዘት ጋር ይበልጥ የሚዛመደውን ለይቶ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ አዋሳኝና ጎረቤት ዞኖች ስምና መገኛ አቅጣጫቸውን መግለጽ አለባቸው፡፡ በተማሪዎች መጽሐፍ በስዕል 1፤2 ላይ የተቀመጠውን በመጠቀም አዋሳኝ ዞኖች ስም በክፍል ውስጥ እንዲዘረዝሩ ማድረግ ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንድያዳብሩ ማድረግ**

ተማሪዎች በካርታ ላይ የዞናቸውንና የእያንዳንዱ የጎረቤት ዞኖች ዋና ከተማ መገኛ እንዲያብራሩ ማድረግ፡፡ በዚህ የተግባር ስራ ተማሪዎች ካርታን ተጠቅመው የዞናቸውንና የእያንዳንዱ ዞን ዋና ከተማ ፍጹማዊ መገኛ እንዲያብራሩ ዕድል መስጠት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች በራሳቸው ፈጠራ ችሎታ የዞናቸውን መገኛ በአንጻራዊ ዘዴ እንዲያሳዩ ማበረታታትና መደገፍ አለባችሁ፡፡

**ተከታታይ ሚዘና**

- በምዕራፉ የተማሩትን የትህምርት ይዘቶች ውስጥ ግልጽ ያልሆነላቸው ካለ ለይተው እገዛ ይደረግላቸው፤

- ተማሪዎች በግልና በቡድን ሆነው በትህምርቱ ይዘት ውሰጥ የተካተቱትን መልመጃዎችና የተግባር ስራዎችን እንዲሰሩ ማድረግ፣ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ደግሞ ማበረታታት ያስፈልጋል፤
- ተማሪዎች የሚያሳዩትን የባህሪይ ለውጥ በተከታታይ መመዝገብና መገምገም፤
- ተማሪዎች በሚሰሩት ስራና የተግባር ስራ ሲያከናውኑ ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

**ተግባር 2.4**

በተማሪዎች መጽሐፍ ውስጥ በሰንጠረዥ 1፤2 ላይ የተቀመጠውን በመጠቀም የኦሮሚያ ዞኖች መገኛ በአራቱ አቅጫዎች ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ሰሜንና ደቡብ በማለት መልስ ይስጡ፡፡ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የኦሮሚያ ካርታ መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነዉ፡፡

**የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ**

**ተግባር 2.1**

**ሀ.እውነት /ሐሰት ጥያቀዎች መልስ**

1. **እውነት** 2. **እውነት** 3. **ሐሰት** 4. **ሐሰት** 5. **እውነት**

**ለ. የምርጫ ጥያቄዎች መልስ**

1. ለ
2. ሐ
3. መ
4. ሐ
5. ሐ
6. መ
7. ሀ
8. ሀ

# ምዕራፍ 3 ተፈጥሮኣዊ አካባቢያችን

ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት… 54

**የምዕራፉ የመማር ዉጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-**

- በአየር ሁኔታና በአየር ንብረት መካከል ያለዉን ልዩነት ይገልጻሉ፣
- በተለያዩ ወቅቶች የሚጠበቁ የአየር ሁኔታዎችን ይገልጻሉ፣
- የዞናችዉን መጠነ-ሙቀት ልዩነት ይመዝናሉ፣
- የዞናችዉን የዝናብ ስርጭት ልዩነት ያወዳድራሉ፣
- የአየር ንብረት ወሳኝ ሁኔታዎችን ይለያሉ፣
- የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ ሀብቶችን ይለያሉ፣
- የተፈጥሮ ሀብት ጥቅሞችን ይገልጻሉ፣
- የተፈጥሮ ሀብት ዉድመትና መንስዔዎችን ይገልጻሉ፣
- መደበኛ እና ሀገር በቀል እዉቀቶችን በመጠቀም የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ሊወሰዱ የሚገቡ እረምጃዎችን ይገልጻሉ፣
- የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅና መንከባከብ ለቀጣይ ትዉልድ የሚኖረዉን ጥቅም ያስረዳሉ፣
- በወረዳቸዉና በትምህርት ቤታቸዉ ብክለትን ለመቀነስ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል አስፈላጊነት ላይ ሀሳብ ይሰጣሉ፣
- ከአካባቢያቸዉ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ቆሻሻን ባልተገባ መንገድ ማስወገድ የሚያስከትለዉን ጉዳት በመረዳት አካባቢን በንጽህና የመያዝ ጥቅምን ይገልጻሉ፡፡

**መግቢያ**

በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች ስለ አየር ሁኔታና አየር ንብረት ልዩነት፤ በተለያዩ ወቅቶች የሚጠበቁ የአየር ሁኔታዎች፤ በዞናቸዉ ዉስጥ ስለሚኖር መጠነ-ሙቀት ልዩነት፤ የዞናቸዉ የዝናብ ስርጭት ሁኔታ፤ የዞናቸዉ የአየር ንብረት ወሳኝ ጉዳዮች፤ የተፈጥሮ እና ሰዉ ሰራሽ ሃብቶች፤ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም፣ የተፈጥሮ ሀብት ውድመትና መንስዔዎች፤ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ፣ በትምህርት ቤታቸዉና በአካባቢያቸዉ ቆሻሻን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል፣ ቆሻሻን ባልተገባ መንገድ የመጣል አሉታዊ ተጽዕኖ አና የአካባቢ ንጽህና ጥቅሞችን ይማራሉ፡፡

## 3.1 የዞናችን የአየር ንብረት

ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት..........12

**የዚህ ርዕስ ትምህርት የመማር ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-**

- በአየር ሁኔታና በአየር ንብረት መካከል ያለዉን ልዩነት ይገልጻሉ፣
- በተለያዩ ወቅቶች የሚጠበቁ የአየር ሁነታዎችን ይገልጻሉ፣
- የዞናቸዉን መጠነ-ሙቀት ልዩነት ይገልጻሉ፣
- የዞናቸዉን የዝናብ ስርጭት ልዩነት ያወዳድራሉ፣
- የዞናቸዉን የአየር ንብረት ቁልፍ ወሳኝ ሁኔታዎችን ይለያሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

**በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት**

በየጊዜው የሚለዋወጥ አየር የአየር ሁኔታ ይባላል፡፡ የአየር ሁኔታ በደቂቃዎች፣ በሰዓታት፣ በቀናት፣ በሣምንታት፣ በወራትና በአመታት የሚለዋወጥ የሙቀት፣ የዝናብ የቅዝቃዜና የመሳሰሉት ሊሆን ይችላል፡፡

የአየር ንብረት ማለት ደግሞ በረጅም ጊዜ ውስጥ ለምሳሌ በአማካይ በሰላሳና ከዚያ በላይ ዓመታት ጊዜ ውስጥ የሚከሰት የአየር ለውጥ ማለት ነው፡፡ የአንድ አካባቢ የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት በመጠነ-ሙቀት፡ በእርጥበት፣ በአየርና በንፋስ ግፊት እና በመሳሰሉት ይገለጻል፡፡

**በተለያዩ ወቅቶች የሚጠበቁ የአየር ሁኔታ ልዩነቶች**

በዓመት ውስጥ አራት ወቅቶች ይገኛሉ፡፡ እነሱም ክረምት፣ ፀደይ፣ በጋና በልግ ይባላሉ፡፡ በእነዚህ ወቅቶች ያለው የአየር ሁኔታ የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ በክረምት ወቅት በአብዛኛው ደመናና ዝናብ ይበዛል፡፡ የበጋ ወቅት ደግሞ በአብዛኛው ደረቃማና ሞቃታማ ይሆናል፡፡ በበልግና ፀደይ ወቅቶች ደግሞ በብዙ ቦታ መጠነኛ ስለሚሆን የአየሩ ሁኔታም መካከለኛ ይሆናል፡፡

**የአየር ንብረትን የሚወስኑ ነገሮች**

የአንድን አካባቢ የአየር ንብረትን እንዲለወጥ የሚያደረጉ ሁኔታዎች የአየር ንብረትን የሚወስኑ ነገሮች ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነዚህም:- የመሬት ከፍታ፣ የኬክሮስ መስመር እና የመሳሰሉናቸው፡፡

ከእነዚህ የአየር ሁኔታ ወሳኝ ሁኔታዎች ውስጥ በአካባቢያችን ይበልጥ ጎልቶ የሚታየው የመሬት ከፍታ ልዩነት ነው፡፡ ለምሳሌ:- የመሬት ከፍታ በጨመረ ቁጥር የዝናብ መጠን የሚጨምር ሲሆን የሙቀት መጠን ደግሞ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ ከዚህ በመነሳት ቦታዎች ደጋ፣ ወይናደጋ እና ቆላ ተብለው ይመደባሉ፡፡

## ቅድመ-ዝግጅት

ይህንን ርዕስ ማስተማር ከመጀመራችሁ በፊት አስፈላጊዉን ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ትምህርት ብቃት ያለዉ እቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ንዑሳን ይዘቶች ላይ ከተለያዩ አጋዥ መጽሃፍት በቂ መረጃ መሰብስብና እራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ይዘቶቹንም ለማስተማር

አግባቢነት ያላቸዉን የትምህርት ማበልጸጊያ መሳርያዎችን ከኣካባቢዉ ማዘጋጀትና ማደራጀት ይገባል፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

የትምህርቱን ይዘት ማስተማር ከማጀመራችሁ በፊት አስፈላጊዉን ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቹዋል፡፡ ትምህርቱንም ለመጀመር ማነቃቃት ያስፈልጋል፡፡ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅና ተማሪዎች እንዲሞክሩ ማድረግ ጠቃሚ ነዉ፡፡ በመቀጠል ከትምህርቱ ርዕስ ጉዳዮች አንጻር በተመደበዉ ክፍለ-ጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ተማሪዎች፡-

በአየር ሁኔታና በአየር ንብረት ላይ በቡድን ተወያይተዉ ለክፍል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፣

በአጠቃላይ በዞናቸዉ የአየር ሁነታን እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ተማሪዎቹ የደረቅና እርጥበት አየር ንብረትን ካርታ ላይ መለየት እንዲችሉ ይርዷቸዉ፡፡ ቀጥሎም ከዞናቸዉ መጠነ-ሙቅት ካርታ ላይ የሙቀት መጠን ልዩነትን መመልከት እንዲችሉ ያብቋቸዉ፡፡

ቀጥሎም ተማሪዎች የዞናቸዉን የአየር ንብረት ቁልፍ ወሳኝ ሁነታዎች ላይ ተወያይተዉ ለክፍል እንዲያቀርቡ ያመቻቹላቸዉ፡፡

በሁሉም የትምህርቱ አርዕስቶች ላይ የተማዎችን ዉይይት እና የሚሰጡትን መልሶች በቅርበት በመከታተል ማስተካከያ እና ግብረ-መልስ ከበቂ ገለጻ ጋር መስጠት፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንዲያዳብሩ ማገዝ**

- ተማሪዎች በቡድን በመሆን በትልቅ ወረቀት ላይ በአየር ሁኔታና አየር ንብረት መካከል ያለዉን ልዩነት ጽፈዉ ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግና በተሻለ ሁኔታ ያቀረቡትን ማበረታታት፣

- ከአየር ንብረት ቁልፍ ወሳኝ ሁኔታዎች ዉስጥ አንዱን ልዩ ችሎታ ላላቸዉ ተማሪዎች በመስጠት በአከባቢዉ አየር ንብረት ላይ የሚኖረዉ ተጽዕኖ ላይ ተወያይተዉ ለክፊል እንዲያቀርቡ በማነሳሳት ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ተማሪዎች በአየር ሁኔታና በአየር ንብረት መካከል ያለዉን ልዩነት መግለጽ መቻላቸዉን መከታተልና ማረጋገጥ፣
- ተማሪዎች የአየር ንብረት ቁልፍ ወሳኝ ሁኔታዎችን መግለጽ መቻላቸዉን ተከታትሎ ግብረ-መልስ መስጠት፣
- ለተማሪዎች በጽሑፍ የቀረቡ የተግባር ጥያቀዎችን እንዲሠሩ መስጠት፣ መምራት፣ መርዳትና ተከታትሎ ግብረ-መልስ መስጠት፣
- የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ዉጤት ተከታትሎ በመመዝገብ ገንቢ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

**ተግባር 3.1**

1. የዝናብ ሁኔታ በመሬት አቀማመጥ (ደጋ፣ ወይናደጋ፣ ቆላ)ና በመሳሰሉት ላይ ተወስኖ ልዩነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ ተማሪዎቹ በሚሰጡት መልስ ላይ የማስተካከያና የማጠናከሪያ ሀሳብ ይስጡዋቸዉ፡፡
2. በደጋ፣ ወይናደጋ፣ ቆላና በመሬት ክፍፍልና በመሳሰሉት ላይ በመመስረት የዝናብ ስጭትም ልዩነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ተማሪዎች ከዞናቸዉ ሁኔታ በመነሳት የሚሰጡት መልስ ላይ የማስተካከያና የማጠናከሪያ ሀሳብ ይስጡዋቸዉ፡፡

# 3.2. የተፈጥሮ ሀብት

ለዚህ ርዕስ ትምህርት የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ..........18

**ከተማሪዎች የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች**

*ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-*

- የተፈጥሮ እና ሰዉ ሰራሽ ሀብቶችን ምንነት ይገልጻሉ፣
- በዞናቸዉ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶችን ይለያሉ፣
- የተፈጥሮ ሀብት ጥቅሞችን ይገልጻሉ፣
- በዞናቸዉ የተፈጥሮ ሀብት ዉድመት፣ መንስዔዎችንና ተጽዕኖያቸዉን ይገልጻሉ፣
- ለቀጣይ ትዉልድ የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅና መንከባከብ የሚኖረዉን ጥቅም ይመሰክራሉ፣
- መደበኛ እና ሀገር በቀል እዉቀቶችን በመጠቀም የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ሊወሰዱ የሚገቡ እረምጃዎችን ይገልጻሉ፣
- የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅና መንከባከብ ለቀጣይ ትዉልድ የሚኖረዉን ጥቅም ያስረዳሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

**የተፈጥሮ እና ሰዉ ሰራሽ ሀብቶች ምንነት**

ሀብት ለኑሮአችን የሚያስፈልጉ ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ተብለው ለሁለት ይከፈላሉ፡፡ የተፈጥሮ ሀብት በተፈጥሮ በአካባቢያችን የሚገኙ ሀብቶች ናቸው፡፡ አነዚህም አየር፣ ውሃ፣ የፀሐይ ብርሃን፣ የተፈጥሮ ነዳጅ፣ እፅዋት፤ እንስሳት፣ አፈር፣ ማእድናት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ሰው ሰራሽ ሀብቶች በሰው ልጆች የተሰሩ ሀብቶች ናቸው፡ ፡ ከሰው ሰራሽ ሀብቶች ውስጥ፡- መኖሪያ ቤቶች፤ የቤት ውስጥ እቃዎች፤

ማሽኖች፤ መኪናዎች፤ ባቡር፤ አውሮፕላን፤ መርከብ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

## የዞናችን የተፈጥሮ ሀብት ጥቅሞችና ትሩፋቶች

የተፈጥሮ ሀብቶች ለምግብ፤ ሀይል ማመንጫና የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለመስራት ይጠቅማሉ፡፡ ሰዎች ምግባቸውን ከእፅዋትና ከእንሰሳት ያገኛሉ፡፡ ከተፈጥሮ ሀብቶች ውስጥ የከሰል ድንጋይ እና የተፈጥሮ ጋዝ ሙቀትና ብርሃን ለመስጠት ይጠቀማሉ፡፡ በመሆኑም የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብ ይገባል፡፡

ለተፈጥሮ ሀብት የሚደረግ እንክባካቤ ሀብቱ እንዳይጎዳና ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግል ለማድረግ ይጠቅማል፡፡

የተፈጥሮ ሀብቶች የተለያዩ ቱሩፋቶችንም ያስገኛል፡፡ ከእነዚህ ቱሩፋቶች ዉስጥ፡-

- የመዝናኛ
- የምርምር
- የሥነ-ውበት እና
- የባህል ቱሩፋቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

ይህንን ርዕስ ማስተማር ከመጀመራችሁ በፊት አስፈላጊዉን ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ትምህርት ብቃት ያለዉ እቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ንዑሳን ይዘቶች ላይ ከተማሪዎች መጽሃፍና ከተለያዩ አጋዥ መጽሃፍት በቂ መረጃ መሰብስብና ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ይዘቶቹንም ለማስተማር አግባቢነት ያላቸዉን የትምህርት መርጃ መሳርያዎችን ለምሳሌ፡- ምስሎች፣ ሥዕሎችና ፖስተሮችን ማዘጋጀትና

ማደራጀት ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአካባቢ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን መጎብኘት ይቻላል፡፡

1. የመማር ማስተማር ዘዴ

ትምህርቱን ከመጀመራችሁ በፊት ተማሪዎችን ማነቃቃት፤ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅና ተማሪዎች እንዲሞክሩ ማድረግ ጠቃሚ ነዉ፡፡ በመቀጠል ከትምህርቱ ርዕስ ጉዳዮች አንጻር በተመደበዉ ክፍለ-ጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ተማሪዎች፡-

ሀ. የተፈጥሮ ሀብቶችና ሰዉ ሰራሽ ሀብቶች ምን እነደሆኑ ተማሪዎች ያላቸዉን ግንዛቤ በቡድን ተወያይተዉ ለክፍል እንዲያቀርቡ በማድረግ ግብረ-መልስ በመስጠት ይጀምሩ፡፡

ለ. በመቀጠል ተማሪዎች በቡድን ተደራጅተዉ በዞናቸዉ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች በመዘርዘር እንዲወያዩበትና ለክፍል እንዲያቀርቡ ያመቻቹላቸዉ፡፡ ተማሪዎች ከሚያቀርቡት ሀሳብ በመነሳት ተጨማሪ ገለጻና ግብረ-መልስ ይስጡ፣

ሐ. በቡድን በመሆን በዞናቸዉ በሚገኙት የተፈጥሮ ሀብቶችና ጥቅሞቻቸዉ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ

መ. ከአከባቢያቸዉ በመነሳት የተፈጥሮ ሀብት ውድመት ምንነት፣ መንስዔዎች፣ ተጽዕኖዎችና የመፍትሔ እርምጃዎች ላይ ተወያይተዉ ለክፍላቸዉ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፣

በሁሉም የትምህርት አርዕስት ላይ የተማሪዎችን ዉይይት እና የሚሰጡትን መልሶች በቅርበት በመከታተል ማስተካከያ እና ግብረ-መልስ ከበቂ ገለጻ ጋር ይስጡ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንዲያዳብሩ ማገዝ**

ተማሪዎች በቡድን በመሆን ከአካባቢዉ ከሚገኙ ነገሮች በአካባቢያቸዉ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ሞዴሎችና ሥዕሎች አዘጋጂተው ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግና በተሻለ ሁኔታ ያቀረቡትን ማነቃቃትና ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ተማሪዎች የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚወክሉና ከትምህርቱ ይዘትና ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ምስሎች፣ ሥዕሎችና ፖስተሮችን ተጠቅመዉ ያላቸዉን ግንዛቤ እንዲገልጹ በማድረግ ገንቢ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡
- ለተማሪዎች በጽሑፍ የቀረቡ የግንዛቤ ጥያቀዎችን፣ የተግባር ጥያቀዎችንና ፕሮጀክቶችን እንዲሠሩ ማድረግ፣ ምልከታ ማድረግ፣ መምራት፣ መርዳትና ተከታትሎ ግብረ-መልስ መስጠት፣
- የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ዉጤት ተከታትሎ በመመዝገብ ገንቢ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

ተግባር 3.3

1. በዞናቸዉ የተለያዩ የተፈጥሮ ሐብቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ዉስጥ ደን፣ የዱር እንስሳት፣ ወንዞች፣ ማዕድናት እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
2. በዞናቸዉ የተለያዩ ሰዉ ሰራሽ ሀብቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ዉስጥ መኖሪያ ቤቶች፣ የቤት ዉስጥ ቁሳቁሶች፣ ማሽኖች፣ መኪናዎች፣ ድልድዮች፣ መንገድ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይችላሉ፡፡

ተግባር 3.4

1. በአንድ ዞን የሚገኙ የዱር እንስሳት በሌሎች ዞኖች ላይኖሩ ይችላሉ። በመሆኑም ተማሪዎች በዞናቸዉ ዉስጥ የሚገኙትንና የሚያዉቁትን የዱር እንስሳት መዘርዘር ይችላሉ።

ተግባር 3.5

1. አግድም በማረስ፣ የዕፅዋቶችን ተረፈ-ምርት በእርሻ መሬት ላይ በመተዉ፣ እረከን በመሥራትና የጎርፍ መዉረጃ ቦይ በማበጀትና የመሳሰሉትን በማድረግ አፈር በጎርፍ እንዳይሸረሸር ማድረግ ይቻላል፡ ፡

## 3.3. የተፈጥሮ ሀብት አስፈላጊነት

ለዚህ ንዑስ ርዕስ የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ............................12

**ከተማሪዎች የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች**

ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኂላ፡-

- የተፈጥሮ ሀብት ጥቅሞችን ይገልጻሉ፣
- የተፈጥሮ ሀብት ውድመትና መንስዔዎችን ይገልጻሉ፣
- መደበኛ እና ሀገር በቀል እዉቀቶችን በመጠቀም የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎችን ይገልጻሉ፣
- የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅና ማንከባከብ ለቀጣይ ትዉልድ የሚኖረዉን ጥቅም ያስረዳሉ።

**ዋና ዋና ነጥቦች**

የተፈጥሮ ሀብት ህይወት ላላቸው ነገሮች በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አፈር፣ ውሃ፣ ደንና የመሳሰሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብና በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል የሰው ልጆችን ኑሮ ለመሻሻል እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

የተፈጥሮ ሀብት የተለያየ ጥቅሞች ያስገኛል ፡፡ እነዚህም፡-

- የገቢ ምንጭ
- የሀይል ምንጭ
- ለውሃና አካባቢ ንጽህና
- የምግብ ምንጭ ለእንሰሳት መጠለያ
- አፈር ለማልማትና እንክባካቤ እና የመሳሰሉት መጥቀስ ይቻላል፡፡

**የተፈጥሮ ሀብቶች ውድመት ምክንያቶችና ተፅዕኖው**

የተፈጥሮ ሀብት ውድመት ማለት በተፈጥሮ ሀብት እንክባካቤና ጥበቃ እጦትና ያለአግባብ በመጠቀም ምክንያት በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት ነው፡፡

ለተፈጥሮ ሀብቶች ውድመት ምክንያት ከሆኑት ነገሮች ዋና ዋናዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- የህዝብ ቁጥር መጨመርና የከተሞች መስፋፋት
- ያለአግባብ መጠቀም
- የደን ምንጠራና ቃጠሎ
- የኢንዱስትሪዎች መስፋፋት
- የአፈር መሸርሸር እጥበትና የመሳሰሉት ናቸው ፡፡

በተፈጥሮ ሀብቶች ውድመት ምክያቶች ሊፈጠሩ ከሚችሉ ተፅዕኖዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፡-

- የጤና ችግር
- ረሃብ
- የኢኮኖሚ ችግር እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

**የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅና መንከባከብ**

**የአፈር እንክባካቤ**

የአፈር እንክብካቤ ዘዴዎች ብዙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-

- አግድም ማረስ
- ችግኝ መትከል
- እርከን መስራት
- በእርሻ መሬት ላይ የዕፅዋት ተረፈ ምርት ባለማቃጠል
- የግጦሽ መሬትን ከሚገባው በላይ አለማስጋጥ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

**የውኃ እንክብካቤ**

ውኃን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መንከባከብ ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ችግኞችን መትከል
- የዝናብ ውሃን በማጠራቀም መጠቀም
- ቆሻሻን  ወደውሃ ባለመጣል
- ውሃን በቁጠባ በመጠቀምና በመሳሰሉት

**የደን እንክብካቤ**

ደንን በተለያዩ ዘዴዎች መንከባከብ የሚንችል ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ  የሚከተሉት ናቸው ፡፡

- ለደን ጥበቃ በማድረግ
- በደን ጥበቃና እክብካቤ ላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማጎልበት

- ችግኝ መትከል
- የደን ጥበቃ እና እንክብካቤን በተመለከተ በገዳ ሥርዓት የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ስራ ላይ ማዋልና የመሳሰሉት ናቸው ፡፡

የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅና መንከባከብ በርካታ ጥቅሞች ያሉት ሲሆን ዋና ዋናዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የተፈጥሮ ሚዛንን ለመጠበቅ፤
- ህይወት ያላቸው ነገሮች እንድቀጥሉ ለማድረግ፤
- ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግና
- ቀጣይነት ላለው ለሰው ልጆች ጥቅም

**ቅድመ-ዝግጅት**

ይህንን ርዕስ ማስተማር ከመጀመራችሁ በፊት አስፈላጊዉን ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ንዑሳን ይዘቶች ላይ ከተማሪዎች መጽሃፍና ከተለያዩ አጋዥ መጽሃፍት በቂ መረጃ መሰብስብና ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ይዘቶቹንም ለማስተማር አግባቢነት ያላቸዉን የትምህርት መርጃ መሳርያዎችን ለምሳሌ፡- ምስሎች፣ ሥዕሎችና ፖስተሮችን ማዘጋጀትና ማደራጀት ይገባል፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

ትምህርቱን ለመጀመር ተማሪዎችን ማነቃቃት፤ የትምህርቱን ይዘት በተመለከተ ተማሪዎች በሁለተኛ ክፍል የአከባቢ ሳይንሰ ትምህርታቸዉ ከተማሩት የሚያስታዉሱትን እንዲናገሩ የማነቃቀያ ጥያቄዎችን መጠየቅና ተማሪዎች እንዲሞክሩ ማድረግ ጠቃሚ ነዉ፡፡ በመቀጠል ከትምህርቱ ርዕስ ጉዳዮች አንጻር በተማሪዎች መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን እንድመልሱ ማድረግ፡፡

ተማሪዎች በጥያቄዎች ላይ የሚሰጡትን መልስ በቅርበት ተከታትለዉ ማስተካከያ በመስጠት ማበረታታት፡፡ በመቀጠል በእያንዳንዱ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ በቂ ገለጻ እና ግብረ-መልስ ይስጡአቸዉ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንዲያዳብሩ ማገዝ**

ተማሪዎች በቡድን በመሆን በአካባቢያቸዉ ከሚገኙት የተፈጥሮ ሀብቶች ሞዴሎችንና ሥዕሎችን አዘጋጅተው ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግና በተሻለ ሁኔታ ያቀረቡትን ማነቃቃትና ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ተማሪዎች የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚወክሉና ከትምህርቱ ይዘትና ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ምስሎች፣ ሥዕሎችና ፖስተሮችን ተጠቅመዉ ያላቸዉን ግንዛቤ እንዲገልጹ በማድረግ ገንቢ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡
- ለተማሪዎች በጽሑፍ የቀረቡ የግንዛቤ ጥያቀዎችን፣ የተግባር ጥያቀዎችንና ፕሮጀክቶችን እንዲሠሩ ማድረግ፣ ምልከታ ማድረግ፣ መምራት፣ መርዳትና ተከታትሎ ግብረ-መልስ መስጠት፣
- የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ዉጤት ተከታትሎ በመመዝገብ ገንቢ ግብረ-መልስ መስጠት

# 3.4 ቆሻሻን ማስወገድ

**ለዚህ ርዕስ የተመደበዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት ……………………..10**

**ከተማሪዎች የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-**

- በወረዳቸዉና በትምህርት ቤታቸዉ ብክለትን ለመቀነስ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል አስፈላጊነት ላይ ሀሳብ ይሰጣሉ፣

**ዋና ዋና ነጥቦች**

ቆሻሻ በደረቅ ወይም በፈሳሽ መልክ ሊኖር ይችላል፡፡ አካባቢያችን ሊበክሉ የሚችሉ የቆሻሻ አይነቶች ከተለያየ ቦታ ሊወጡ ይችላሉ ፡፡

በአካባቢያችን ከሚስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ውስጥ ቆሻሻን ባልተገባ ቦታ መጣል አንዱ ነው ፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ቆሻሻን ከአካባቢ ማስወገድ አስፈላጊ ነው፡፡

በዚህ ርዕስ ተማሪዎች ቆሻሻን መቀነስ ከሚቻልባቸዉ መንገዶች ዉስጥ አንዱ የወዳደቁ ቆሸሸዎችን በድጋሚ ጥቅም ላይ በማዋል መሆኑን ይማራሉ፡፡ በመሆኑም የሚከተሉትን መልካም ተሞክሮዎች ተግባራዊ በማድረግ ቆሻሻን ማስወገድ ይቻላል፡፡ እነዚህም መልካም ተግባራት፡-

- ቆሻሻ የሚወገድባቸውን የተለያዩ ቦታዎች በማዘጋጀት መጠቀም፣
- የእፅዋት ተረፈ ምርትን በኮምፖስት መልክ ለመዳበሪያነት መጠቀም፣
- የተለያየ የፕላስትክ እና ወረቀቶችን እንደገና መጠቀም፣
- ከተለያዩ ቦታዎች የሚወጡት ፍሳሽ ቆሻሻዎችን በአግባቡ ማስወገድና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

**ቅደመ-ዝግጅት**

ይህንን ርዕስ ማስተማር ከመጀመሪዎ በፊት አስፈላጊዉን ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ንዑሳን ይዘቶች ላይ ከተማሪዎች መጽሐፍና ከተለያዩ አጋዥ መጽሐፍት በቂ መረጃ መሰብስብና እራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

ይዘቶቹንም ለማስተማር አግባቢነት ያላቸዉን የትምህርቱ መርጃ መሳሪያዎችን ለምሳሌ፡- ቆሻሻ በማስወገድ ረገድ በአከባቢዉ የሚስተዋሉትን

መልካምና መልካም ያልሆኑ ተግባራትን የሚያሳዩ ምስሎች፣ ሥዕሎችና ፖስተሮችን ማዘጋጀትና ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

ትምህርቱን ለመጀመር አስፈላጊዉን ዝግጅት ካደረጉ በኋላ፤ ተማሪዎችን በማነቃቃት፤ የትምህርቱን ይዘት በተመለከተ በዚህ ጉዳይ ላይ ተማሪዎች በሁለተኛ ክፍል የአከባቢ ሳይንሰ ትምህርታቸዉ ከተማሩት የሚያስታዉሱትን እንዲናገሩ የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅና ተማሪዎች እንዲሞክሩ ማድረግ ጠቃሚ ነዉ፡፡ በመቀጠል ከትምህርቱ ርዕስ ጉዳዮች አንጻር በተመደበዉ ክፍለ-ጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ተማሪዎች የሚከተሉትን የግንዛቤ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ በማድረግ ገንቢ ግብረ-መልስ በመስጠት ትመህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ ያድርጉ፡፡

በመቀጠል በትምህርት ቤታቸዉም ይሁን በመኖሪያ ሰፈራቸዉ ቆሻሻ በልተገባ ሲጣል አከባቢን እንደሚበክል እንድገነዘቡ ማድረግ፡፡

ቀጥሎም ተማሪዎች አከባቢያቸዉን የሚበክሉ የቆሻሻ አይነቶች ላይ በቡድን ተወያይተዉ በሪፖርት መልክ ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

የተማሪዎችን የግንዛቤ ደርጃ ከለዩ በኋላ በቆሻሻ አወጋገድ ዙሪያ መልካምና መልካም ያልሆኑ ተግባራት ላይ ይበልጥ ግንዛቤያቸዉን እንዲያጎለብቱ ተግባራቱን በሚከተለዉ ሰንጠረዥ መልክ በወረቀት ወይም በሰሌዳ ላይ በመጻፍ ለተማሪዎቹ ማሳየት፡፡

| መልካም የሆነ የቆሻሻ አወጋገድ ተግባራት | መልካም ያልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ ተግባራት |
|---|---|
| ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ማዘጋጀት | ባልሆነ ቦታ ቆሻሻ መጣል |
| የተለያዩ ቆሻሻዎችና ፕላስትኮችን በአልባሌ ቦታ አለመጣል | የተለያዩ ቆሻሻዎችና ፕላስትኮችን በየቦታዉ መጣል |
| ወረቀቶችን ቀዳዶ በየቦታዉ አለመጣል | ወራቀቶችንና ከቤት የሚወጡ ቆሻሻዎችን በየቦታዉ መጣል |
| በድጋሚ ለሌላ አገልግሎት ሊዉሉ የሚችሉ ቆሻሻዎችን እንደገና መጠቃም | በድጋሚ ለሌላ አገልግሎት ሊዉሉ የሚችሉ ቆሻሻዎችን በየቦታዉ መጣል |
| ከፋብሪካዎች የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻን በአካባቢ ላይ እንዳይለቀቅ ማድረግ | ከፋብሪዎች የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻን በአካባቢ ላይ መልቀቅ |

በተጨማሪም የአከባቢ ንጽህና መጠበቅ ጤናማና አምራች ዜጋ ለማፍራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለዉ ተማሪዎቹን ያስገንዝቡ፡፡ አከባቢያችንን ልበክሉ የሚችሉ ቆሻሻዎች ከመኖሪያ ቤቶች፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከፋብሪካዎች እና ከመሳሰሉት ሊወጡ እንደሚችሉ በመግለጽ፤ በአከባቢያቸዉ ቆሻሻን በማስወገድ ረገድ የተለያዩ መልካም ተሞክሮዎችን እንዲለማመዱ ማበረታታት፡፡ በዚህ መሰረት ቆሻሻን በየፈርጁ መሰብሰብ በተዘጋጀላቸዉ ቦታ ብቻ ማስወገድ፤ ለሌላ አገልግሎት ሊዉሉ የሚችሉትን በድጋሚ መጠቀም፤ መበስበስ የሚችሉ የዕፅዋት ተረፈ ምርቶችን ለአፈር በመዳበሪያነት መጠቀም እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንዲያዳብሩ ማገዝ**

የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ ለማጎልበት ተማሪዎችን በማነቃቃት የቆሻሻ ማጠራቀሚያ እቃዎችን በራሳቸዉ ሰርተዉ በትምህርት ቤታቸዉ እንዲጠቀሙበት ማድረግ፡፡ በተሸለ ሁኔታ ሰርተዉ ያቀረቡትንና በቆሻሻ አወጋገድ መልካም ተሞክሮ ያሳዩትን ተማሪዎች ተከታትሎ በክፍል ዉስጥ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ተማሪዎች በግንዛቤ ጥያቄዎች፣ በተግባር ጥያቄዎች እና በመማር ማስተማር ህደት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የሚሰጡትን መልስ በመከታተል ምን ያህል የትምህርቱን ይዘት እንደተረዱ መገምገምና ተገቢዉን ግብረ-መልስ መስጠት፣
- የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ዉጤት ተከታትሎ በመመዝገብ ገንቢ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

**የተግባር ጥያቄ መልስ**

**ተግባር 3.6**

አከባቢን ሊበክሉ ከሚችሉ ቆሻሻዎች ዉስጥ መልሰን እንደገና መጠቀም ከሚንችላቸዉ ዉስጥ፡- ፕላስቲኮች፣ የተጣሉ ቁርጥራጭ ብረቶችና ቆርቆሮዎች፣ የተለያዩ የመጠጥ ጣርሙሶች እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለሌላ አገልግሎት ሊዉሉ ከሚችሉት ደግሞ ፕላስትክ የዉሃ ጣርሙሶች፣ የተቀደዱ ወረቀቶች፣ የእንጨት ስብርባሪዎችና ብስባሽ የእፅዋት ተረፈ ምርቶች እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

## 3.5 ቆሻሻ ተገቢ ባልሆነ መንገድ የመጣል ተፅዕኖ

**ለዚህ ርዕስ የተመደበዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት ..............................2**

**ከተማርዎች የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-**

ከአካባቢያቸዉ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ቆሻሻን ባልተገባ መንገድ መጣል የሚያስከትለዉን ጉዳት በመረዳት አካባቢን በንጽህና የመያዝ ጥቅምን ይገልጻሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

ተገቢ ባልሆነ መንገድ ቆሻሻን መጣል በጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡ የሚጣለው ቆሻሻ አፈር፣ ውሃ እና አየር በመበከል በአካባቢ ላይ ጉዳት ያደርሳል፡፡ በዚህ መንገድ ልደርሱ የሚችሉትን የጤናና ተያያዥ ችግሮችን ተማሪዎች እንዲያዉቁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ባልተገባ መንገድ በሚጣል ቆሻሻ ሊደርስ የሚችለውን ችግር በማስቀረት የአካባቢያችንን ንጽህና መጠበቅ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

**ቅደመ-ዝግጅት**

ይህንን ርዕስ ማስተማር ከመጀመራችሁ በፊት አስፈላጊዉን ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ንዑሳን ይዘቶች ላይ ከተማሪዎች መፅሐፍ፣ ከተለያዩ አጋዥ መፅሐፍት በቂ መረጃ መሰብስብና ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ይዘቶቹንም ለማሰተማር አግባቢነት ያላቸዉን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ለምሳሌ፡- ቆሻሻ ባልተገባ መንገድ የመጣል ድርግቶችንና ተፅዕኖአቸዉን የሚያሳዩ ምስሎች፣ ሥዕሎችና ፖስተሮችን ማዘጋጀትና ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

ትምህርቱን ለመጀመር አስፈላጊዉን ዝግጅት ካደረጉ በኋላ፤ ተማሪዎችን በማነቃቃት፤ የትምህርቱን ይዘት በተመለከተ በዚህ ጉዳይ ላይ ተማሪዎች ያላቸዉን ግንዛቤ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማነቃቀት ጠቃሚ ነዉ፡፡ በመቀጠል ከትምህርቱ ርዕሰ ጉዳዮች አንጻር በተመደበዉ ክፍለ ጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ተማሪዎች በተማሪ መፅሐፍ ዉስጥ የቀረቡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን፤ ለምሳሌ፡- ቆሻሻን በየቦታ የመጣል ተፅዕኖ ላይ ተማሪዎች የመስክ ምልከታ አድርገዉ ለክፍል እንዲያቀርቡ በማድረግ ከመልሳቸው በመነሳት ገንቢ ግብረ-መልስ በመስጠት ትመህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ ማድረግ፡፡

በመቀጠል በትምህርት ቤታቸዉም ሆነ በመኖሪያ ሰፈራቸዉ ቆሻሻ በልተገባ መንገድ ሲጣል አከባቢን እንደሚበክል በማሳሰብ መልካም የቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴዎች ላይ በቂ ገለጻ በመስጠት ተማሪዎች እንደየአቅማቸዉ እነዚህን ተሞክሮዎች እንዲያዳብሩ ያስገንዝቧቸዉ፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ እንዲያዳብሩ ማገዝ**

የተማሪዎች የፈጠራ ችሎታ ለማጎልበት ተማሪዎችን በማነቃቃት ቆሻሻን ባልተገባ ቦታ መጣል የሚያስከትለዉን አሉታዊ ተፅዕኖ ላይ በደረጃቸዉ ምርምር አድርገዉ የምርምር ዉጤቱን እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ ሀደቱንም በመከታተል በተሸለ ሁኔታ ያቀረቡትን ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ተማሪዎች በግንዛቤ ጥያቄዎች፣ በተግባር ጥያቄዎች እና በመማር ማስተማር ሕደት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የሚሰጡትን መልስ በመከታተል ምን ያህል የትምህርቱን ይዘት እንደተረዱ በመገምገም ተገቢዉን ግብረ-መልስ መስጠት፣
- የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ዉጤት ተከታትሎ በመመዝገብ ገንቢ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

**የምዕራፉ የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ**

**እዉነት ወይም ሐሰት**

1. እዉነት 2. እዉነት 3. እዉነት 4. እዉነት 5. ሐሰት

**ምርጫ**

6. ሀ 7. ሐ 8. ለ 9. መ 10. መ

# ምዕራፍ 4 ማህበራዊ አከባቢያችን

ለምዕራፉ የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ……………………..54

ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

- የባህል ምንነት ይገልፁ፤
- በዞናቸዉ ውስጥ የሚጠቀሙ ባህላዊ ተግባራትን ይለያሉ፤
- በዞናቸው ውስጥ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመንከባከብ የሚረዱ ባህሎችን ተግባራትን ይዘረዝራሉ፤
- የባህል ብዝሃነትን ያደንቃሉ፤
- ለባህል ብዝሃነት ምክንያት የሆኑትን ይገልጻሉ፤
- የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ምንነትን ይገልጻሉ፤
- የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ይዘረዝራሉ፤
- የገበያ ምንነትን ይገልጻሉ፤
- የገበያ ጥቅሞችን ይዘረዝራሉ፤
- የመጓጓዣ ምንነትን ይገልጻሉ፤
- የመጓጓዣ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፡፡

**መግቢያ**

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ትኩረት የሚሰጣቸው ነጥቦች የአከባቢ ማህበረሰብ ፤ የባህል ምንነት፤የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት እና የባህል ብዝሃነት ናቸው ፡፡ እንድሁም በዞናቸው ከሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ውስጥ በስፋት ለገበያ አገልግሎት የሚጠቀሙትን እና የገበያ ጥቅሞችን ይማራሉ፡፡በተጨማሪም በዞናቸው ለመጓጓዣነት የሚጠቀሙበትን ለይቶ ይማራሉ፡፡

# 4.1. የአከባቢያችን የባህል ብዝሃነት

ለዚህ ትምህርት የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ……………..……20

- ተማሪዎች በአከባቢያቸው የሚገኙ የባህል ብዝሃነትን ይገልጻሉ፤
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመንከባከብ የሚረዱ ባህላዊ ተግባራቶችን ይለያሉ፤
- በአከባቢያቸው የሚገኙ የባህል ብዝሃነትን ያደንቃሉ፤

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በዚህ የትምህርት ይዘት ተማሪዎች ስለባህል እና የባህል ጥቅሞችን ፣ የኅብረተሰብ የአኗኗር ሁኔታ ፣የባህል ብዝሃነት ምክንያቶችን ይማራሉ፡፡ እንደዚሁም በዞናቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ለመንከባከብ የሚረዱ የኅብረተሰቡ ባህለዊ እሴቶችን ይማራሉ ፡፡

ይህንን የትምህርት ይዘት ለማስተማር ከተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ውስጥ ምቹ የሆነውን በመምረጥ መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ከተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች የቡድን ስራ፣ማብራሪያ መስጠት እና ተማሪዎችን ሁለት በሁለት በማደራጀት እንዲወያዩ ማድረግ የትምህርት ይዘቱን ለማስተማር የሚረዳ የመማር ማስተማር ዘዴን መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በዚህ የትምህርት ይዘት ውስጥ ትኩረት የሚፈልጉ የዞናቸው የባህል ምንነት እና የባህል ብዝሃነት ናቸው፡፡ የባህል መገለጫ የሆኑ ነገሮች የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ የአምልኮና የእርቅ ስርዓቶችንም በስፋት ይማራሉ፡ ፡

መምህራን ተጨማሪ መጽሐፍትን በማንበብ በባህል ብዝሃነት ዙሪያ ግንዛቤያቸውን ማዳበር አስፈላግ ይሆናል፡፡ ይህንን የትምህርት ይዘት

ለማስተማር ስዕሎችን፣ፖስተሮችን እና ለሎች ጠቃሚ የትምህርት መርጃ መሳርያዎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው።

የባህል ብዝሃነት ሊፈጠር የቻለው በምን ምክንያት እንደሆነ ተማሪዎችን በጥያቄ እና መልስ አማካኝነት በመጠየቅ የሚሰተጡትን መልስ ማቀናጀት አስፈላጊ ነው። በመጨረሻም የተለያዩ ኅብረተሰቦች ለረጅም ግዜ በተለያዩ ቦታዎች በቋምነት በምኖሩበት ወቅት ያካበቱት ልምዶች ለባህል ብዝሃነት መፈጠር ምክንያት መሆኑን ማጠቃለያ መስጠት አስፈላግ ነዉ።

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

መምህራን ይህንን የትምህርት ይዘት ማስተማር ከመጀመራቸው በፍት ቅደመ ዝግጅት ማድረግ አሰፈላጊ ነው። የተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎት በጥያቄ እና መልስ ዘዴ ማጎልበት ተገቢ ይሆናል። በዚህ የትምህርት ይዘት ውስጥ የተለያዩ ጥያቄዎች መጠየቅ። ለምሳሌ

ሀ.ባህል በምን በምን ይገለጻል;

ለ. ለባህል ብዝሃነት ምክንያት የሆኑ ነገሮች ምንድን ናቸው;

ሐ. ለአከባቢ ጥበቃ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያላቸው ከኅብረተሰብ ባህሎች ውስጥ ጥቅቶችን ጥቀስ የሚሉ ናቸው።

ተማሪዎች ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ ከሰጡ በኃላ የዕለቱን ትምህርት ማካሄድ ትችላላችሁ። በመቀጠል ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት በተለያዩ ኅብረተሰብ መካካል በባህል ብዝሃነት ምክንያት የሚፀባረቁ ልዩቶችን እና ተቀራራቢነታቸዉን እርስ በእርሳቸው እንዲወያዩበት ዕድል መስጠት።

መምህራን ተማሪዎች እርስ በራሳቸው ውይይት ሲያካሄዱ በትኩረት መከታተል አለባቸው። የእያንዳንዱ ተማሪዎች ሪፖርት በመገምገም ትክክል ያልሆኑ ሐሳቦችን ማስተካከል አስፈላጊ ነው ። በወይይታቸው ውስጥ ስህተት

ካለ ማስተካከያ ፣ገንብ እና ትክክለኛ ግብረ መልስ በመስጠት ማጠቃለል አስፈላጊ ይሆናል ።

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ መደገፍ**

የተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸው እንዲዳብር በአከባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች ሞደሎችን በመስራት እና የአከባቢያቸውን ባህል የሚያንጸባርቁ ልብሶችን ለብሰው የተለያዩ ዝግጅቶችን እንዲያዘጋጁ ዕድል መስጠት። በዝግጅቱ ላይ ትክክለኛ የኅብረተሰቡን ባህል የሚያንጸባርቁ ትይንት እንዲያቀርቡ በቂ ልምምድ እንዲያደርጉ መከታተል አስፈላጊ ነው ።

**ተከታታይ ምዘና**

የትምህርቱን ርዕሰና አላማ መሰረት በማድረግ በአካባቢያቸው የሚገኙ የባህልና የአባገዳ ልብሶች ስዕል፣ ፎቶግራፍ እና ፖስተሮች ማዘጋጀት። ተማሪዎችን በጥያቄና መልስ የመማር ፍላጎታቸውን ማጠናከር አስፈላጊ ነው፡ ፡ ተማሪዎችን በቡድን እና በግል ሁሉንም የተግባር ስራዎችን እና መልመጃዎችን እንድሰሩ ማድርግ። ተማሪዎች የሚያቀርቡትን ሪፖርት መገምገም እና ገንቢ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው።

**ተግባር 4.1**

የዚህ ተግባር ጥያቄዎች በዞናችሁ ውስጥ የሚገኙ ባህሎች ላይ ያተኩራል። ተማሪዎች እንደየዞናቸው የተለያዩ መልስ ወይም ሐሳቦችን ሊሰጡ ይችላሉ፡ ፡ በመጨረሻ ላይ ይህ ሊሆን የቻለበት ከባህል ብዛሃነት ምክንያት መሆኑን መምህራን የማጠቃለያ ሐሳብ መስጠት አስፈላጊ ነው።

**ተግባር 4.2**

ተማሪዎች በዞናቸው ውስጥ ታዋቂ የሆኑ የባህል ምግቦችን በዘርዝር አንድ በአንድ ማብራሪያ እንድሰጡበት ማድረግ። በመጨረሻም የማጠቃለያ ሐሳብ መስጠት አስፈላጊ ይሆናል።

**ተግባር 4.3**

የተለያዩ ኅብረተሰብ የተለያዩ ባህላዊ የግጭት አፈታት ልማዶች አሉአቸዉ፡፡ ስለዝህም ተማሪዎች ቤተሰቦቻቸውን በአከባቢያቸዉ ግጭትን እንዴት እንደሚፈቱ ጠይቀው በክፍል ውስጥ በቡድን ሚና በመጫወት እንድያቀርቡ ማድረግ ፡፡

# 4.2 የዞንናችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠ የክፍለ ጊዜ ብዛት ………………4

ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባው የመማር ብቃት

- የኢኮኖሚ እንቅሰቃሴን ይገልጻሉ፤
- የዞናቸውን የኢኮኖሚ እንቅሰቃሴን ይናገራሉ፤
- የዞናቸውን ዋነኛ የኢኮኖሚ እንቅሰቃሴና ጥቅም ይዘረዝራሉ፤
- የኢኮኖሚ እንቅሰቃሴ በአከባቢ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚደርሱትን ጉዳቶች ይዘርዝራሉ፤
- የግብርና ስራ ጥቅምን ይዘርዝራሉ፤
- የፋብሪካ ጥቅምን ይገልፃሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በዚህ ርዕስ ውስጥ የኢኮኖሚ እንቅሰቃሴ ዘርፎችን በስፋት እንድማሩ ተዘጋጅቷል፡፡ መምህራን ይህንን የትምህርት ይዘት ማስተማር ከመጀመራቸው በፍት ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አሰፈላጊ ነው ፡፡ የተማሪዎች የትምህርት ፍላጎት በጥያቄ እና መልስ ዘዴ ማጎልበት ተገቢ ነዉ፡፡ ይህንን የትምህርት ይዘት ለማስተማር ምቹ የሆነውን የመማር ማስተማር ዘዴ የቡድን ስራ፣ሁለት በሁለት በማደራጀት በጥያቄና መልስ፣ በፕሮጀክት ስራ እና ከመሳሰሉት በመምረጥ ማስተማር ተገቢ ነው፡፡ ተማሪዎች በአከባቢያቸው

የሚገኙ ኅብረተሰብ በስፋት የሚሳተፉበትን የኢኮኖሚ ዘርፎችን እንድለዩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

- እለታዊ የትምህርት እቅድ ማዘጋጀት፤
- የተለያዩ አጋዥ መጽሐፍት ማንበብ፤
- በዞናቸዉ ውስጥ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችን ስም እና መገኛቸውን መለየት፡፡

ከተለያዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ጥያቄ እና መልስ፤ የቡድን ስራ፤ ሠርቶ ማሳያ እና ከመሳሰሉት ውስጥ መምረጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች የአከባቢያቸው ኅብረተሰብ በስፋት የሚሳተፉበትን የኢኮኖሚ ዘርፎችን በማቀናጀት ሪፖርት እንድያቀርቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በባህላዊ እና ዘመናዊ መንገዶች የሚከናወኑ የግብርና ስራ ልዩነታቸውን መዘርዘር አስፈላጊ ነው፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

መምህራን ይህንን የትምህርት ይዘት ማስተማር ከመጀመራቸው በፍት ቅደመ ዝግጅት ማድረግ አሰፈላጊ ነው ፡፡ በዕለታዊ ዕቅዳቸው ውስጥ የተማሪዎች የትምህርት ፍላጎት በጥያቄ እና መልስ ዘዴ ማጎልበት ተገቢ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ በዚህ የትምህርት ይዘት ውስጥ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ፡

ሀ. የኢኮኖሚ እንቅሰቃሴ ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. የኢኮኖሚ እንቅሰቃሴ ጥቅሞች ምንድን ናቸው? የሚሉት ልሆን ይችላል፡፡

በመቀጠል ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት እርስ በራሳቸው ሲወያዩ መከታተል አሰፈላጊ ነው፡፡ በመጨረሻም የሚስተካከሉ ሀሳቦች ካሉ በማስተካከል ገንቢ ግብረ መልስ ይሰጥበት፡፡ ተማሪዎች ስለ ኢኮኖሚ

እንቅሰቃሴ ግንዛቤ እንዲያዳብሩ በማድረግ መልሶቻቸውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ሁሉንም የክፍል ተማሪዎችን በማሳተፍ ትክክኛውን መላስ መለየት፡፡

በመጨረሻም ንግድ እና ኢንዱስትሪ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደሚመደቡ ማስረዳት፡፡ እንድሁም የኢንዱስትሪ እንቅሰቃሴ ባህላዊ እና ዘመናዊ ተብለው እንደምመደብ ማስረዳት፡፡ በዞናቸው የሚገኙ ባህላዊ እና ዘመናዊ ኢንዱስትሪ እንድዘረዝሩ ዕድል መስጠት፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ መደገፍ**

ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸው እና ግንዛቤያቸውን እንዲያዳብሩ በአከባቢያቸው ፋብርካዎች ካሉ እንድጎበኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላግ ነዉ፡፡

**ተከታታይ ሚዘና**

ተማሪዎች በቡድን እና በግል ሁሉንም የተግባር ስራዎችን እና መልመጃዎችን እንድሰሩ ማድርግ፡፡ ተማሪዎች የሚያቀርቡትን ሪፖርት መገምገም እና ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች በቡድን እና በግል ሪፖርት ሲያቀርቡ መከታተል እና የሚያሳዩትን የባህሪይ ለውጥ ግንዛቤን መመዝገብ እና ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው ፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

**ተግባር 4.5**

1. ተማሪዎች በአከባቢያቸው የሚገኙ በህላዊ የማጓጓዣ አገልግሎት በመስጠት የሚታወቁን እንድዘረዝሩ በማድረግ ተጨማሪ ማብራሪያ ይሰጥበት፡፡

2. ተማሪዎች በአከባቢያቸው ከሚገኙ የማጓጓዣ ዓይነቶች ውስጥ ሰዉና ዕቃን የማጓጓዝ አገልግሎት በመስጠት የሚታወቁትን እንድዘረዝሩ ማድረግ፡፡
3. ተማሪዎች በአከባቢያቸው የሚገኙና ለገበያ የሚቀርቡ የተፈጥሮ ሀብቶችን ቤታሰቦቻቸዉን በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞች እንድያቀርቡ ማድረግና በመጨረሻ ማጠቃለያ መስጠት፡፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

**ተግባር 4.6**

የተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅቃሴዎች በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚያደርሱ ጉዳቶች ብዙ ናቸው፡፡ እንደ ዞናቸው በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጉዳት በማደረስ የሚታወቁ የኢኮኖሚ እንቅቃሴዎች በክፍል ውስጥ ሪፖርት እንድያቀርቡ ማድረግ፡፡ መምህራን ከሪፖርታቸው በኃላ የማጠናከሪያ ሐሳብ በመስጠት ማጠቃለል አስፈላጊ ነው ፡፡

**የምዕራፍ አራት ጥያቄዎች መልስ**

**ሀ. እውነት/ ውሸት ጥያቄዎች መልስ**

1. እዉነት 2. እዉነት 3. እውነት
4. እውነት 5. እውነት

**ለ.የምርጫ ጥያቄዎች መልስ**

6. መ 7. ሐ 8. መ 9. ለ 10. መ

# መዕራፍ 5 ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ጉዳዮች

የተመደበዉ የክፍለ ጊዜ ብዛት………………………………... 30

የምዕራፉ የመማር ዉጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኂላ፡-

- የትራፊክ ደንቦችን በመለየት ይተገብራሉ፤
- የኤች አይ ቪ እና የኤድስ ልዩነት ይለያሉ፣
- የኤድስ በሽታ ምልክቶችን ይረዳሉ፡፡

**መግቢያ**

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች የትራፊክ ደንቦችና አተገባበራቸዉ፤ ኤች አይ ቪ እና የኤድስ ምንነትና ልዩነት፤ የኤድስ በሽታ ምልክቶችን ይማራሉ፡ ፡

## 5.1 በመንገድ አጠቃቀም ላይ የሚደረግ ጥንቃቄ

ተማሪዎች ልደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኂላ፡-

- የመንገድ ትራፊክ ደንቦችን በመለየት ይተገብራሉ

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በዚህ ንዑስ ርዕስ ውስጥ ተማሪዎች የመንገድ ትራፊክ አደጋዎችን ለመከላከል ሊከተሉ ስለሚገባቸዉ ጥንቃቄዎች ይማራሉ፡፡ ይህም ማለት በመንገድ ላይ ሲጓዙ ከተለያዩ የትራፊክ አደጋዎች ራሳቸዉን ለመከላከል የሚችሉባቸዉ ጥንቃቄዎች ማለት ነው፡፡

በመንገድ ላይ የተለያዩ የትራፊክ አደጋዎች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ

ዋና ዋናዎቹ፡-

- መንገድ ሲሻገሩ ግራ እና ቀኝ አቅጣጫን በማየት በጥንቃቄ ያለመሻገር፣
- የአሽከርካሪዎች ጥንቃቄ አለማድረግ፣
- እንሰሳትን ያለጥንቃቄ መንገድ ላይ መንዳት፣
- በከባድ ዝናብ ምክንያት በድንገት የሚደርስ ጎርፍ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

የመንገድ ትራፊክ ደንቦችን አለማክበር ለተለያዩ አደጋዎች ያጋልጠናል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የህይወት መጥፋት፣
- የአካል መጉደል፣
- የሀብት መውደም እና የመሳሰሉት ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

የመንገድ የትራፊክ አደጋዎችን የሚከተሉትን የትራፍክ ደንቦቸን በማክበርና ተግባራዊ በማድረግ መከላከል ይቻላል፡፡

- በመኪና መንገድ ላይ ስንሄድ ግራ አቅጣጫን በመያዝ መሄድ፤
- በመኪና መንገድ ላይ አለመጫወት
- የትራፊክ ምልክቶችን ተገንዝቦ ተግባራዊ ማድረግ
- ለእግረኛ በተፈቀደ መንገድ (በዜብራ ላይ) ብቻ መሻገር

**ቅደመ-ዝግጅት**

ይህንን ርዕስ ማስተማር ከመጀመራችሁ በፊት አስፈላጊዉን ዝግጅት ማድረግ፡፡ በርዕሱ ጉዳዩ ላይ የተለያዩ መጽሐፍትን በመጠቀም በቂ መረጃ መሰብሰብና መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

ትምህርቱን ተጨባጭና ምቹ ለማድረግ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ለምሳሌ ሥዕሎችንና የትራፊክ አደጋ ዉጤቶችንና የትራፊክ ደንቦችን የሚያሳዩ ፖስተሮችን ቀደም ብሎ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

ትምህርቱን ለመጀመር አስፈላጊዉን ዝግጅት ካደረጉ በኋላ፤ ተማሪዎችን በማነቃቃት፤ የትምህርቱን ይዘት በተመለከተ በዚህ ጉዳይ ላይ ተማሪዎች ያላቸዉን ግንዛቤ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማነቃቃት ጠቃሚ ነዉ፡፡ ለምሳሌ የትርፊክ አደጋ በቤተሰብና በልጆች ላይ በሚያስከትለዉ ጉዳት ላይ ተማሪዎች የሚያዉቁትን እንዲዘረዝሩ ማድርግ ያስፈልጋል፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች በጥንድ ሆነዉ በትራፊክ ደንቦች ላይ ተወያይተዉ የውይይታቸዉን ዉጤት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል፡፡ ተማሪዎቹ በሚሰጡት መልስ መሰረት ገንቢ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከትምህርቱ ርዕስ ጉዳዮች አንፃር በተመደበዉ ክፍለ ጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ተማሪዎች በተማሪዎች መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በማድረግ ተማሪዎቹ በይዘቶቹ ላይ ሊጨብጡ የሚገባቸዉ አንኳር ነጥቦች ላይ ገለጻ ያድርጉላቸዉ፡፡

በትምህርቱ ይዘት መሰረት የትራፊክ አደጋዎችንና ደንቦችን ግንዛቤ ልያበለጽጉ የሚችሉ ሥዕሎችን፣ ፎቶግራፎችንና ፖስተሮችን በመጠቀም ተማሪዎቹ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ያሰፈልጋል፡፡

ከዚህም ዉጪ የተወሰኑ ተማሪዎች እንደ ትራፊክ ፖሊስ ድርሻ ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ በመኪና መንገድ ላይ የሚጫወቱ ህጻናት ድርሻ በመዉሰድ በትወና መልክ እንድያሳዩ በማድረግ የትራፊክ ደንብን ያለማክበር እንዴት ለአደጋ እንደሚያጋልጥ እንዲረዱ ተጨማሪ በመብራራት ማጠቃለያ ሀሳብ መስጠት፡፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማበረታታት**

የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ ለማጎልበት ተማርዎችን በማነቃቃት በአከባቢያቸዉ ከሚገኙ ነገሮች የትራፊክ ደንቦችን የሚያመለክቱ መሳሪያዎችን ሠርተዉ እንዲያቀርቡ በማድረግ ህደቱንም በመከታተል በተሸለ ሁኔታ ሠርተዉ ያቀረቡትን ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ተማሪዎች በግንዛቤ ጥያቄዎች፣ በተግባር ጥያቄዎች እና በመማር ማስተማር ሕደት በሚቀርቡ ጥያቄዎችና መልሶች በመከታተል ምን ያህል የትምህርቱን ይዘት እንደተረዱ በመገምገም ተገቢዉን ግብረ-መልስ መስጠት፣
- የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ዉጤት ተከታትሎ በመመዝገብ ገንቢ ግብረ-መልስ መስጠት

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

**ተግባር 5.1**

1. ትክክለኛ የሆነ መንገድ ይዞ አለመጓዝ፣ተገቢ ባልሆነ ቦታ መንገድ ማቋረጥ፤

   ጠጥቶ ማሽከርከር፣ በመንገድ ላይ መጫወት፤

   ለእገረኛ በተፈቀደ (በዜብራ መንገድ) ምልክት አለመጠቀም እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

2. የራስን ትክክለኛ መንገድ ይዞ መጓዝ፣

   ለእገረኛ በተፈቀደ (በዘብራ) ምልክት ብቻ መጠቀም፣ የመንገድ ግራና ቀኝ አቀጣጫን በደንብ በማየት በጥንቃቄ መንገድ መሻገር

3. በመንገድ ላይ ሲንሄድ የግራ እጅን አቅጣጫ በመያዝ መጓዝ

## 5.2 ኤች አይ አቪ /ኤድስ

ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-

- የኤች አይ ቪ እና የኤድስ ልዩነትን ይለያሉ፣
- የኤድስ በሽታ ምልክቶችን ይረዳሉ፡፡

**ዋና ዋና ነጥቦች**

በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች በኤች አይ ቪ እና በኤድስ መካከል ያለዉን ልዩነት ይማራሉ፡፡ በተጨማሪም በኤድስ በሽታ የተያዙ ሰዎች ምን ምን ምልክቶችን እንደሚያሳዩ ግንዛቤ ያገኛሉ፡፡ ይህንንም ለማስተማር በትምህርቱ ይዘት ላይ ተማሪዎች በጥንድና በቡድን እንዲወያዩ እና በዋና ዋና ይዘቶች ላይ ገለጻ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

ኤች አይ ቪ ማለት ነጭ የደም ህዋስን በመጉዳት ኤድስ የሚባል በሽታን የሚያስከትል ቫይረስ መሆኑን፤ ነጭ የደም ህዋስ ደግሞ ሰውነታችንን ከበሽታ የሚከላከሉ ስሆኑ ህዋሶቹ ሲጎዱ የሰውነታችን በሽታን የመከላከል ብቃት በእጅጉ እንደሚጎዳ ማስረዳት፡፡

በሌላ በኩል ኤድስ ደግሞ በኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ምክንያት የምመጣ በሽታ መሆኑንና እስከ አሁን ድረስ መድሃኒት ያልተገኘለት፤ በበሽታዉ የተያዘ ሰው ሊድን እንደማይችል ተማሪዎቹ ሊረዱ ይገባል፡፡

የኤድስ በሽታ ቫይረሱ ካለበት ሰው ወደ ሌላ ሰው በተለያየ መንገዶች እንደምተላለፍና ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-

- በደም ንክኪ
- የተለያዩ ስለት ያላቸውን ነገሮች በጋራ በመጠቀም
- በቫይረሱ ከተጠቃች እናት ጡት በማጥባት፤
- በእርግዝና እና በወሊድ ጊዜ በቫይረሱ ከተጠቃች እናት ወደ ህፃን ልተላለፍ ይችላል፡፡

በለላ በኩል የኤች አይ ቪ ቫይረስ በመጨባበጥ፣ አብሮ በመጫወት፣ አብሮ በመማር፣ የተለያዩ ዝግጅቶችን አብሮ በመካፈል፣ አብሮ በመብላት እና በመሳሰሉት መንገዶች ሊተላለፍ እነደማይችል ግንዛቤ ሊወሰዱ ይገባል፡፡

በኤድስ በሽታ የተያዙ ሰዎች ምንም ዓይነት ምልክት ሳያሳዩ ነገር ግን ኤች አይ ቪ ቫይረስን ማስተላለፍ ይችላላ፡፡

በኤድስ በሽታ የተያዙ ሰዎች በበሽታው መያዛቸው የሚረጋገጠዉ የደም ምርመራ ሲያደርጉ ብቻ ነው፡፡ በህደት ግን በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች የሚከተሉትን ምልክቶችን ማሳየት ይጀምራሉ፤

- የሰውነት ሙቀት በተከታታይ መጨመር
- ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የራስ ምታትና ደረቅ ሳል
- የሰውነት ክብደት በፍጥነት መቀነስ
- ኃይል ማጣትና የድካም ስሜት መሰማት
- ተቅማጥ
- የአፍ ውስጥ ቁስለትና የመሳሰሉት

**ቅደመ-ዝግጅት**

ይህንን ርዕስ ማስተማር ከመጀመራችሁ በፊት አስፈላጊዉን ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ከተለያዩ አጋዥ መጽሐፍት በቂ መረጃ በመሰብስብ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

ትምህርቱን ተጨባጭና ምቹ ለማድረግ የመርጃ መሳሪያዎችን በኤች.አይ.ቪ ኤድስ ዙርያ የተዘጋጁ ምስሎችን፣ ሥዕሎችንና ፖስተሮችን ቀደም ብሎ ማሰባሰብና ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ**

ትምህርቱን ለመጀመር አስፈላጊዉን ዝግጅት ካደረጉ በኂላ፤ ተማሪዎችን በማነቃቃት፤ በትምህርቱ ይዘት ላይ ተማሪዎች ያላቸዉን ግንዛቤ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማነቃቃት አስፈላግ ነዉ፡፡ ለምሳሌ በኤች.አይ.ቪ እና በኤድስ መካከል ያለዉ ልዩነት ላይ ተማሪዎች በጥንድ ሆነዉ በመወያየት ያላቸዉን ግንዛቤ እንድለዋወጡ በማድረግ መጀመር ይቻላል፡፡ ተማሪዎቹ በሚሰጡት መልስ መሰረት ገንቢ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከትምህርቱ ርዕሰ ጉዳዮች አንጻር በተመደበዉ ክፍለ-ጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት በተማሪዎች መጽሓፍ ዉስጥ የቀረቡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በማድረግ አጠቃላይ ይዘቶች ላይ ሊጨብጡ የሚገባቸዉን እዉቀት እንድያገኙ ማድረግ ነዉ፡፡

ከዚህም ሌላ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት በኤድስ በሽታ የተያዙ ሰዎች የሚያሳዩትን ምልክቶች በዝርዝር እንዲያቀርቡ በማድረግ በተሸለ ሁኔታ ያቀረቡትን በማበረታታት በትምህርቱ አብይ ይዘቶች ላይ ገለፃ በመስጠት ተማሪዎች ከቫይረሱ ራሳቸዉን እንዲጠብቁ በቂ ምክር መስጠት ያስፈልጋል፡
፡

**ተማሪዎች የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማበረታታት**

የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ ለማጎልበት በትልቅ ወረቀት ላይ የኤድስ በሽታ ምልክቶችን በዝርዝር ጽፈዉ እንዲያቀርቡና መሰል ተግባራትን በመስጠት መበረታታት፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ተማሪዎች በግንዛቤ ጥያቄዎች፣ በተግባር ጥያቄዎች እና በመማር ማስተማር ሕደት በሚቀርቡ ጥያቄዎችና መልሶች በመከታተል ምን ያህል የትምህርቱን ይዘት እንደተረዱ በመገምገም ተገቢዉን ግብረ-መልስ መስጠት፣
- በግልና በቡድን የሚሰሩ ተግባራትን በቅርበት በመከታተልና ግብረ-መልስ መስጠት፣
- የእያንዳንዱን ተማሪ የመማር ዉጤት ተከታትሎ በመመዝገብና ገንቢ ግብረ-መልስ መስጠት

**የኤች. ኤ. ቭ/ኤድስ በሽታ መከላከያ መንገዶች:-**

- ያለተመረመረ ደም ለሌሎች ሰዎች አለመስጠት/አለመዉሰድ፤
- ስለታማ የሆኑ ነገሮችን በጋራ አለመጠቀም፤
- የደም ንክክ አለማድረግና የመሳሰሉት መሆናቸዉን ለተማሪዎች መስገንዘብ፡ ፡

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

**ተግባር 5.2**

1. በኤች. አይ .ቪ. እና በኤድስ መካከል ያለውን ልዩነት፤ ኤች አይ ቪ ቫይረስ ነጭ የደም ህዋሶችን በመጉዳት ኤድስ የሚባል በሽታን የሚያስከትል ቫይረስ ሲሆን ኤድስ ደግሞ በኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ምክንያት የምመጣና እስከአሁን ድረስ መድሃኒት ያልተገኘለት በሽታ ነዉ፡፡
2. በኤድስ በሽታ የተያዘ ሰዉ በጤና ተቋማ በመሄድ የእድሜ ማራዘሚያ መድሀኒት መዉሰድ አለበት፡፡
3. የኤች. አይ.ቭ. ቫይረስ መተላለፍያ መንገዶች በደም ንክኪ፤ የተለያዩ ስለት ያላቸው ነገሮችን በጋራ በመጠቀም፤ በቫይረሱ ከተጠቃች እናት ጡት በማጥባት፤ በወሊድ ጊዜ በቫይረሱ ከተጠቃች እናት ወደሚወለደዉ ህፃን ይተላለፋል፡፡

**የምዕራፍ 5 የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ**

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. ሐሰት
5. ሐሰት

የምርጫ ጥያቄዎች መልስ

6. መ 7. ለ 8. መ

# የአካባቢ ሳይንስ መርሃ ትምህርት

# 3ኛ ክፍል

| የመማር ብቃት | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ዘዴዎች | ግምገማ |
|---|---|---|---|
| **3ኛ ክፍል፣ ምዕራፍ አንድ**<br>• ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግብና መጠጥን በመለየት ሀሳብ ይሰጣሉ፤<br>• አራቱን የምግብ ምድቦች ይለያሉ፤<br>• የምግብ ብክለትን ለመከላከል የሚወሰዱ ቀላል ዘዴዎችን ይለያሉ፤<br>• ጋስ፣ ፈሳሽና ጠጣር የሆኑ ነገሮች ፍቺና ባህሪያትን ይለያሉ፤<br>• የንፅህና መጠበቂያ ዘዴዎችን ይገልፃሉ፤<br>• የብርሃን ጥቅምን ይገልፃሉ፡፡ | ምዕራፍ አንድ ምግብና የቤተሰብ ጤና (የክፍለ ግዜ ብዛት 42)<br>1.1. ምግብና ጤንነት<br>1.2. የምግብ ጥቅም<br>• የምግብ ምድቦች (የጥራጥሬ እህል፣ የስጋ ፣ የወተትና የአታክልትና የፍርፍሬ ምድብ)<br>• ለምግብ ብክለት ምክንያቶች<br>1.3. የግል ንፅህና<br>• የግል ንፅህናን ለምን እንጠብቃለን<br>• የግል ንፅህናን ባለመጠበቅ በሌሎች | • ተማሪዎች መፅሐፍን እንድያነቡ ማድረግ<br>• በውይይት፣ በገለፃና በማሳየት ማስተማር<br>• ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል ቀለል ያሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤ በሰፊ ወረቀት ላይ የተለያዩ ምግቦችን ሥዕል በማንሳት ተማሪዎች የሚያዉቁትን እንድመድቡ ማበረታታት<br>• ተማሪዎች ለምግብ ብክለት መነሻ የሚሆኑ ነገሮችን እንድጠይቁና እንድወያዩ ማድረግ፤ለምሳሌ እጅ አለመታጠብ<br>• ተማሪዎች በጤናኛና ታማሚ ሰዎች መካከል ያለዉ ልዩነት ምን እንደሆነ እንድወያዩ ማድረግ፤<br>• ተማሪዎች በጋስ፣ ፈሳሽና ጠጣር መካከል ያለዉን ልዩነት | • ተማሪዎች ምግቦችን በየምድባቸዉ እንድመድቡ ጥያቄዎችን መጠየቅና እንድመልሱ ማሳተፍ፤<br>• ተማሪዎች ለምግብ ብክለት መነሻ የሚሆኑ ነገሮች ላይ ውይየት ሲያደርጉ መከታተል፤<br>• የተማሪዎችን አፈፃፃምና ተሳትፎ መመዝገብ<br>• የተማሪዎችን የመማር ብቃት ለማሻሻል አስፈላጊዉን ግብረ-መልስ መስጠት፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ሰዎች ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት<br>• በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች<br>• ጤናኛና ታማሚ የሆኑ ሰዎችን ማነፃፀር<br>• ለታማሚ ሰዎች የሚደረጉ ትኩረትና እንክብካቤ<br>1.4. የጋስ፣ ፈሳሽና ጠጣር የሆኑ ነገሮች ፍዝካላዊ ለውጥ<br>1.5. የብርሃን ጥቅ | ለመረዳት በቡድን እንደወያዩ ማድረግ፤<br>• ተማሪዎች የብርሃን ምንጭና ጥቅም እንድዘረዝሩ በቤት ስራ መልክ መስጠትና ሰርተዉ እንድያመጡ ማድረግ፤ ለምሳሌ ፀሓይ፣ ጨረቃ፣ ኮከብ፣ ሻማ፣ ባቲሪ፣ አምፑል መሆናቸዉና የብርሃን ጥቅም ደግሞ ለማየት፣ ተክሎች ምግባቸዉን ለማዘጋጀትና ለእድገትና ለሃይል ምንጭነት መሆኑን እንድገልፁ ማድረግ። | • ተማሪዎች የብርሃንን ጥቅም በሚተነትኑበት ግዜ ያለቸዉ እዉቀት ምን ያህል እንደሆነ መገምገም። |

| የመማር ብቃት | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ዘዴዎች | ግምገማ |
|---|---|---|---|
| **3ኛ ክፍል፣ ምዕራፍ ሁለት**<br>▪ አቅጣጫዎችን የመለየት ችሎታን ያዳብራሉ፤<br>▪ ካርታን በመጠቀም ሰዎችን የማገናኘት ችሎታን ያዳብራሉ፤ | ምዕራፍ ሁለት፤ መገኛ<br>(የክፍለ ግዜ ብዛት 34)<br>2.1. የዞናችን መገኛ<br>▪ አንፃራዊ መገኛ፤<br>▪ ፍፁማዊ መገኛ፤ | ▪ ተማሪዎች ስለኬንትሮስና ኬክሮስ መስመሮች የሚያዉቁትን እንድናገሩ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች የዞናቸዉን አንፃራዊ መገኛን እንድናገሩ መጠየቅ፤ | ▪ ተማሪዎች ለጥያቄዎች የሚሰጡትን መልሶች መመልከት፤<br>▪ ተማሪዎች የዞናቸዉና ሌሎች ቦታዎች መገኛ ለመለየት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ▪ አንፃራዊ መገኛን ይገልፃሉ፤<br>▪ ፍፁማዊ መገኛን ይገልፃሉ፤<br>▪ የዞናቸዉን አንፃራዊ መገኛ ይገልፃሉ፤<br>▪ የዞናቸዉን ፍፁማዊ መገኛ ይገልፃሉ፤<br>▪ የኬንትሮስና ኬክሮስ መስመሮችን በመጠቀም የአንድን ቦታ መገኛ በካርታ ላይ ያሳያሉ፤<br>▪ ኬንትሮስና የኬክሮስ መስመሮችን በመጠቀም ታዋቂ የሆኑ ቦታዎችን ያሳያሉ፤<br>ካርታን በመጠቀም በዞናቸዉ ውስጥ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችን ለማሳየት ይችላሉ፡፡ | ▪ የዞናችን አንፃራዊ መገኛ ምንነት፤<br>▪ የዞናችን ፍፁማዊ መገኛ ምንነት፤<br>▪ በዞናችን ውስጥ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎች መገኛ፤<br>የጎረቤት ዞኖች ስምና መገኛቸዉ፤ | ▪ ተማሪዎች ኬንትሮስና ኬክሮስ መስመሮችን በመጠቀም የዞናቸዉን መገኛ በካርታ ላይ እንድያሳዩ ማሳተፍ፤<br>▪ ተማሪዎች የተሰጠዉን የአንድ ቦታ መገኛን ኬንትሮስና ኬክሮስ ማስመሮችን በመጠቀም እንድለዩ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች ዞናቸዉንና ጎረቤት ዞኖችን በካርታ ላይ እንድያሳዩ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች የካርታ አጠቃቀምን በትክክል እንድያጎለብቱ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች እንድያቀርቡ ማድረግ፤ | ያሳዩትን ማሻሻል መከታተል፤<br>▪ ተማሪዎች ሥራቸዉን በሚያቀርቡበት ጊዜ በትክክል ማቅረባቸዉን መከታተል፤<br>▪ ተማሪዎች መገኛን ለመግለፅ የሚያደርጉትን ተሳትፎ መከታተል፤<br>▪ ለተማሪዎች ተሳትፎ ግብረ መልስ መስጠት፤<br>▪ ተከታታይ የሆነ ግምገማ ማካሄድ፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ▪ ተማሪዎች በወረዳቸዉ ውስጥ የሚገኙ ታዋቂ ቦታዎችን ጠይቀዉ እንድመጡ የቤት ሥራ መስጠት | |

| **የመማር ብቃት** | **ይዘቶች** | **የመማር ማስተማር ዘዴዎች** | **ግምገማ** |
|---|---|---|---|
| **3ኛ ክፍል፣ ምዕራፍ ሦስት**<br>• የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ ልዩነት ላይ ውይይት ያደርጋሉ፤<br>• በተለያዩ ወቅት ውስጥ የሚታይ የአየር ሁኔታ ልዩነቶችን ይገልፃሉ፤<br>• የዞናቸዉን የአየር ሁኔታ ልዩነትን ይገመግማሉ፤<br>• የዞናቸዉን የዝናብ ስርጭትን በማወዳደር ይገልፃሉ፤<br>የዞናቸዉ የአየር ሁኔታን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን ይለያሉ፤ | **ምዕራፍ ሦስት**<br>**ተፈጥሮአዊ አከባቢ**<br>(*የክፍለ ግዜ ብዛት 54*)<br><br>3.1 የዞናችን የአየር ንብረት<br><br>• የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታ ልዩነት<br>• የአየር ንብረትን የሚቆጣጠሩ ይዘቶች<br>3.2. የተፈጥሮ ሀብት | • ተማሪዎች ስለአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን እንድናገሩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች ስለዞናቸዉ አጠቃላይ የአየር ሁኔታን እንድገልፁ ማድረግ.<br>• ተማሪዎች በተዘጋጀዉ ካርታ ላይ የዞናቸዉን የዝናብና የአየር ሁኔታን ማሳየት እንድችሉ ማብቃት.<br>• ተማሪዎች በካርታ ላይ በዞናቸዉ የአየር ሁኔታ ልዩነቶችን እንድያሳዩ ማድረግ | • የተማሪዎችን የመልስ አሰጣጥ መከታተል፤<br>• የአየር ንብረትና የአየር ሁኔታን ልዩነት በትክክል መረዳታቸዉን መከታተል፤.<br>• ተማሪዎች የሙቀትና ዝናብ መጠንን ከካርታ ላይ ማናበብ እንድችሉ ማድረግ፤<br>• የተማሪዎችን መልስና ሀሳብ በመመዝገብ የግንባታ ግብረ መልስ መስጠት፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • ለተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ ሀብቶች ትርጓሜ ይሰጣሉ፤<br>በዞናቸዉ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን በመለየት ጠቀሜታቸዉንም ይለያሉ፤<br>• በዞናቸዉ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ብክነት መንስኤዎችና የሚከሰቱ ችግሮችን ይለያሉ፤<br>• በዞናቸዉ ውስጥ በተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀምና እንክብካቤ ላይ ህብረተሰቡ ያላቸዉ ሀገር በቀል እዉቀቶች ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፤<br>• የተፈጥሮ ሀብቶችን በማንከባከብና ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ይረዳሉ፤<br>• በወረዳቸዉና በትምህርት ቤታቸዉ ውስጥ ብክለት የሚቀነስባቸዉን መንገዶችና | • የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ ሀብት ምንነት<br>• የተፈጥሮ ሀብት (ማዕድናትና የዱር እንስሳት)<br>• በዞናቸዉ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት መጠቀምና ዋጋ መስጠት<br>3.3 የተፈጥሮ ሀብት መኖርና<br>ለዞናቸዉ እድገት ያለዉ ጠቀሜታ<br>• በዞናችን ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት ብክነት መንስኤዎችና የሚከሰቱ ችግሮች<br>• በዞናቸዉ ውስጥ በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና እንክብካቤ ላይ ህብረተሰቡ | • ተማሪዎች የአየር ሁኔታን የሚቆጣጠሩ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ እንድወያዩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች ከተወያዩ በኂላ ያገኙትን እዉቀት ለክፍል ተማሪዎች እንደያቀርቡ ማድረግ.<br>• ለተማሪዎች ስለ ሳምንታዊ የአየር ሁኔታ አሳይመንት እንድሰሩ ማድረግ.<br>• ተማሪዎች የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ ሀብቶች ምን ማለት እንደሆኑ እንድገልፁ መጠየቅ<br>• ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ በዞናቸዉ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት (የዱር እንስሳትና ማዕድናትን) በመጥራት እንድወያዩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ በዞናቸዉ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት (የዱር እንስሳትና ማዕድናትን) አጠቃቀምና | • ተከታታይ ምዘና ማካሄድ፤<br>• ለተማሪዎች አስቸጋሪ ለሆኑ ሀሳቦች በውይይታቸዉ ወቅት የሚትጠብቀዉን መግለፅና መብራሪያ መስጠት፤<br>• ተማሪዎች ውይይት ከመጀመራቸዉ በፍት አቅጣጫ የሚያሳዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• በውይይት ወቅት በክፍል ውስጥ በመዘዋወር የተማሪዎችን ተሳትፎ መከታተልና ሁሉም መሳተፋቸዉን ማረጋገጥ፤<br>• በውይይት ወቅት በተሰጠዉ ርዕስ ላይ መተኮራቸዉን ማረጋገጥ፤<br>• ተማሪዎች እርስ በራሳቸዉ እንድወያዩና |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ንብረትን መልሰዉ ለአገልግሎት ማዋል ምን እንደሆነ ሀሳብ ይሰጣሉ፤<br>• ትክክለኛ የቆሻሻ አወጋገድና ንፅህናን መጠበቅ ያለዉ ጠቀሜታን ይገልፃሉ፡፡ | ያላቸዉ ሀገር በቀል እዉቀቶች<br>• በዞናችን ውስጥ የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብና መቆጣጠር ያለዉ ጠቀሜታ<br>3.3 በዞናቸዉ ውስጥ ቆሻሻን ለማስወገድ የሚጠቀሙ ጥሩና መጥፎ ተግባራት.<br>3.4 ትክክል ያልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ የሚያስከትለዉ ተፅዕኖ | ዋጋ መስጠት ላይ እንድወያዩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች የተፈጥሮ ሀብት ብክነት ማለት ምን እንደሆነ እንድገልፁ ማድረግ | የሚያዉቁትን እንድነጋገሩ ማድረግ፡፡ |

| የመማር ብቃት | ይዘቶች | የመማር ማስተማር ዘዴዎች | ግምገማ |
|---|---|---|---|
| 3ኛ ክፍል፣ምዕራፍ አራት<br>ህብረተሰባዊ አከባቢ<br>▪ የባህል ትርጉም ይሰጣሉ፤<br>▪ በዞናቸዉ የሚከናወኑ ባህላዊ እንቅስቃሴዎችን ይገልፃሉ፤<br>▪ በዞናቸዉ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅ የሚውሉ የባህል ዓይነቶችን/ እንቅስቃሴዎችን ይለያሉ፤<br>▪ የባህል ልዩነቶችን ያደንቃሉ፤<br>▪ የአየር ንብረት በዞናቸዉ በሚገኘዉ ባህሎች ላይ የሚያመጣዉን ተፅዕኖ ይገልፃሉ፤<br>▪ የዞናቸዉን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይገልፃሉ፤ | ምዕራፍ አራት<br>ህብረተሰባዊ አከባቢ<br>(*የክፍለ ግዜ ብዛት 54*<br>4.1 የባህል ልዩነት<br>▪ የባህል ትርጉምና ምሳሌዎች<br>▪ የዞናቸዉ የተለያዩ የባህል፤ መገለጫዎች (የአለባበስ፣ አመጋገብና የግጭት አፈታት)<br>▪ በዞናቸዉ የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅና ለማንከባከብ የሚያገለግሉ ባህሎች፤<br>▪ በዞናቸዉ የሚታወቁ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች፤ | ▪ ተማሪዎች የባህል ምንነት እንድናገሩ መጠየቅ፤<br>▪ ተማሪዎች በዞናቸዉ ውስጥ የሚከናወኑ ባህላዊ ተግበሮችን ከሸማግሌዎች በመጠየቅ ለክፍል ተማሪዎች እንድያቀርቡ ማድረገግ፤<br>▪ በክፍል ውስጥ ሽማግሌዎችን በመጋበዝ በዞናቸዉ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅ የሚረዱ ባህላዊ ክንውኖችን ለተማሪዎች እንድያስተምሩ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች በዞናቸዉ ውስጥ በሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ በህላዊ ክንውኖች ምን እንደሆኑ የቤት ሥራ | • በርዕሶች ላይ መወያየት እና የተገኘዉን ውጤት መግለፅ፤<br>• ወይይት ከመጀመራቸዉ በፍት የተለያዩ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ማቅረብ፤<br>• በተማሪዎች ውይይትግዜ በክፍል ውስጥ በመዘዋወር ሁሉም ተማሪዎች እኩል መሳተፋቸዉንና በርዕሱ ላይ በትክክል መወያየታቸዉን ማረጋገጥ፤<br>• ተማሪዎች እየተማሩ ባሉት ርዕስ ላይ ብቻ ትኩረት እንድሰጡ ማድረግ፤<br>• ተማሪዎች ጥያቄ እየተጠያየቁ፣ ሀሳብ እየተሰጣጡና |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ▪ የዞናቸዉን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያለዉ ተፅዕኖ ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፤<br>▪ በዞናቸዉ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ትርጉምና ጥቅማቸዉን እንድሁም በገበያ ላይ ያለዉ ተፈላግነት ምን እንደሆነ ይገልፃሉ፤ | ▪ የዞናቸዉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያለዉ ጉዳት፤<br>▪ በዞናቸዉ ለገበያ የሚዉሉ የተፈጥሮ ሀብት፤<br>▪ የተፈጥሮ ሀብትና ለገበያ የሚቀርቡ ውጤቶች፤ | ሰርተዉ እንድመጡ መስጠት፤<br>▪ የዞናቸዉ የኢኮኖሚ እንቅስዋሴዎች ምን እንደሆኑ እንድዘረዝሩ ተማሪዎችን መጠየቅ፤<br>▪ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት የተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ምን እንደሆነ መጠየቅ፤<br>▪ ተማሪዎች በዞናቸዉ ውስጥ የሚገኙና ለገበያ የሚቀርቡ የተፈጥሮ ሀብቶችና ጥቅማቸዉ ምን ምን እንደሆኑ ለሌሎች ተማሪዎች እንድያቀርቡ ማድረግ፤<br>▪ ተማሪዎች በዞናቸዉ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችና ጥቅማቸዉን እንድሁም በገበያ ላይ ያለዉ ተፈላግነት በቡድን | በተክክል እየተደማመጡ መሆናቸዉን መከታተልና እርምት መስጠት፤<br>• ውይይቱ በጥቅት ተማሪዎች እንዳይዋጥና በተቻለ መጠን ሁሉም ተማሪዎች ሀሳበቸዉን እንድገልፁ በማድረግ መከታተል፤<br>• በውይይት ወቅት በቂ የሆነ ሀሳብ እንድያመነጩ የሚረዱ ግልፅ የሆኑ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ለተማሪዎች መስጠት፤<br>• ለማጠቃለያ የሚሆኑ ዋና ዋና ሀሳቦችን ለተማሪዎች በጥቁር ሳሌዳ ላይ መፃፍና ሰርተዉ ላቀረቡት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በመወያየት ለሌሎች ታማሪዎች እንድያቀርቡ ማድረግ፤ | የቤት ሥራዎች ትክክለኛ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት፤<br>• ተማሪዎች በእኛ አስተሳሰብ ብቻ እንድመሩ ከማድረግ መቆጠብ ያስፈልጋል |

| **የመማር ብቃት** | **ይዘቶች** | **የመማር ማስተማር ዘዴዎች** | **ግምገማ** |
|---|---|---|---|
| **3ኛ ክፍል፣ ምዕራፍ አምስት ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ጉዳዮች**<br>• የትራፊክ ደንቦችን መግለፅና መፈፀም ይችላሉ፤ .<br>• የኤች. አይ. ቭ. ና ኤድስን በመለየት የኤድስ ምልክቶችን ያጠናሉ/ ይገልፃሉ፡፡ | ምዕራፍ አምስት ልዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች<br>(የክፍለ ግዜ ብዛት *30* )<br>5.1. የመንገድ ላይ መረጃዎች<br>5.2. ኤች. አይ. ቭ./ኤድስ | • የትራፊክ አደጋዎችበቤተሰብ ልጆች ላይ ልያደር የሚችለዉን ጉዳቶች ምንም እንደሆኑ ተማሪዎችን መጠየ<br>• እንደ የትራፊክ ፖሊስ በመንገድ ላይ ኳስ የሚጫወቱ ልጆችን ለማስተማር ሚና በመጫወት እንድያሳዩ አድርጉ፤<br>• የኤች. አይ. ቭ. ቫይረስና በኤድስ ላይ በቂ መብራሪያ መስጠት፡፡ | • የተማሪዎችን ገለፃ መከታተል<br>• መረጃ እንዴት እንደሚተነተን እንድገልፁ ማድረግና በመጨረሻም ግብረ ማልስ መስጠት፡፡ |